ምዕራፍ ሦስት

የመጋቢነትና የሽማግሌዎች አመራር

በዚህ ክፍል ሊነሡ የሚገባቸውን ጥያቄዎች ቀደም ብለን ጠቃቅሰናቸዋል። አሁን ግን በቅድሚያ መሠረታዊ የሆኑ ነገሮችን በማስቀመጥ ወደ መጽሐፍ ቅዱሳዊውና ሚዛናዊው አመለካከት እንድናዘነብል የሚረዱ ነጥቦችን እንመለከታለን። ቤተ ክርስቲያንን ማን ይምራት ወይም ያስተዳድራት? ሽማግሌዎች ወይስ መጋቢ? የሚለውንም አከራካሪ ነጥብ በግልጽ የምንዳስስበት ይሆናል።

3.1 መጋቢነት/ፓስተርነት (Pastor/Shepherd)

መጋቢነት ማለትም ፓስተር እየተባለ በእንግሊዝኛ ትርጉሙ ሲነገር የምንሰማው ቃል በወቅቱ ባለው ትርጉም በአማርኛ የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ውስጥ አይገኝም። ዳሩ ግን በመጀመሪያ የአማርኛ ትርጉሙ እንዴት እንደ ተሰጠው ባላውቅም ምናልባት ትክክለኛ ስያሜ አልያዘም ይሆናል የሚል አመለካከት አለኝ።

መጋቢነት ጸጋ ነው ወይስ በትምህርት ከዚያም በሹመት የሚሰጥ ሥልጣን? በሉቃስ 12፥42 እና 16፥1-3 ውስጥ «መጋቢ» ተብሎ የተጠቀሰው ቃል የሥራ መሪ ወይም ማናጀር (Steward or Manager) ማለት ሲሆን ፓስተር የሚለውን የመንፈሳዊ ሹመት ተግባር ግን ፈጽሞ አይተካም። በእንግሊዘኛም ይሁን በግሪኩ ትርጉም ከፍተኛ ልዩነት እንዳላቸው ግልጽ ነው። በግሪኩ ይህኛው ቃል (Οικονομος) ሲሆን በኤፌሶን 4፥11 ውስጥ የተጠቀሰው ፓስተር/እረኛ ግን (Ποιμενας) ነው። በ1951 ዓ. ም. የታተመው የከሳቴ ብርሃን ተሰማ የአማርኛ መዝገበ ቃላት መጋቢ የሚለውን ቃል በጥሬ ቃሉ ሲፈታው፥ «አዛዥ፥ ሞግዚት፥ ምግብን አቅራቢ፥ አስተዳዳሪ፥ አስተንታኝ» ብሎ ይፈታዋል። ይህም ቢሆን በዚህ ስፍራ እኛ የምንጠቀምበትን መሠረታዊ ትርጉሙን ያዛባና የቤተ መንግሥት ወይም የከበርቴዎች ባለሟል ያደርገዋል። ለነገሩ ይህ መጋቢ/መመገብ (Feed) የሚለውን የእንግሊዝኛ ቃል የሚጠቅስ

ይመስላል። ሆኖም ግን ፓስተር/መጋቢ ወይም እረኛ የሚባለውን በፍጹም አይተካም።

ለምሳሌ፡- በዮሐንስ ወንጌል 21፥ 15-17 ውስጥ የተጠቀሱት ቃላት «አሰማራ፥ ጠብቅ፥ እና አሰማራ» የሚሉት በእንግሊዝኛ አንድ ዓይነት ቃላት ሲሆኑ፥ የአዲስ ኪዳን መጽሐፍ ቅዱስ መጀመሪያ በተጻፈበት በግሪክኛው ቋንቋ ግን እንደ አማርኛው በቁጥር 15 እና 17 ያሉት ከቁጥር 16 /Ποιμαινε =Poimen «ፖኤሜን» / ማለትም በእንግሊዝኛ (tend like a Shepherd or keep sheep) ከሚለው ትንሽ ይለያያሉ። ሆኖም ቁጥር 15 እና 17 በግሪኩ /βοσκε =Boske «ቦስኬ» / የሚለው ቃል (Feed/Tend) ተብሎ ትርጉም ተሰጥቶታል።

በእርግጥ «The Expanded Vines» በሚባለው መዝገበ ቃላት ውስጥ በግሪኩ ያለው ቃል [Ποιμην = (Poimen)] በመኖሩ ለእረኛ/ፓስተር እንደሚከተለው ሰፍሯል። «በጎችን የሚጠብቅና የሚንከባከብ እረኛ» ሆኖ የሚመግብ ብቻ አለመሆኑን በግልጽ አሳይቷል። ይህ የመምራትና የመመገብ ድርሻ በሐዋርያት ሥራ 20፥28 ከሚሊጢን ወደ ኤፌሶን ሐዋርያው ጳውሎስ ልኮ ካስመጣቸው የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች የአገልግሎት ድርሻ ጋር ተመሳሳይ መሆኑን በቀላሉ መገንዘብ እንችላለን።

በእንግሊዝኛውና በሌሎች የአማርኛ ትርጉሞች መጽሐፍ ቅዱስ እንደዚህ ይላል፥

"Take heed to yourselves and to all the flock, in which the Holy Spirit has made you guardians=(Episcopoi/Bishops), to feed (Poimenien=to shepherd or pastor) the church of the Lord which he obtained with his own blood." (RSV).

"Keep watch over yourselves and over all the flock, of which the Holy Spirit has made you overseers, to shepherd the church of God/Lord that he obtained with the blood of his own Son."[NRSV].

ይህም ማለት በአዲሱ መጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም፡- «መንፈስ ቅዱስ እናንተን የመንጋው ጠባቂ አድርጎ ሾሞአችኋል፥ እንግዲህ ለራሳችሁና ለመንጋው ተጠንቀቁ፥ ጌታ በገዛ ደሙ የዋጃትን ቤተ ክርስቲያን ጠብቁ» ሲል፥

በሕያው ቃል ደግሞ፡- «ክርስቶስ በደሙ የዋጀትን ቤተ ክርስቲያኑን እንድትጠብቁ መንፈስ ቅዱስ እናንተን መሪዎች አድርጎ ሰለ ሾማችሁ፥ ምዕመናንን በሚገባ የመጠበቅና የመንከባከብ ኃላፊነት አለባችሁ» ይላል። በሌሎቹም ትርጉሞች እንደዚሁ ነው።

ይኸው ጥቅስ በድሮው ትርጉም «በገዛ ደሙ የዋጀትን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ትጠብቁአት ዘንድ መንፈስ ቅዱስ እናንተን ጳጳሳት (Episkopos, or Overseers) አድርጎ ለሾመበት ለመንጋው ሁሉና ለራሳችሁ ተጠንቀቁ» ይላል።

ይህም ተግባር የሽማግሌዎች መሆኑን እንደ ገና በ1ኛ ጴጥሮስ 5፥2-3 ውስጥ እናገኛለን፤

"Tend the flock of God that is your charge, not by constraint but willingly, not for shameful gain but eagerly, not as domineering over those in your charge but being examples to the flock." [RSV] ይላል።

በአዲሱ ትርጉም፥ «በዐደራ የተሰጣችሁን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ፤ መንጋውን የምትጠብቁትም በግድ ሳይሆን እግዚአብሔር በሚፈልገው ዓይነት፥ በፈቃደኝነት ይሁን፤ ለገንዘብ በመስገብገብ ሳይሆን ለማገልገል ባላችሁ ፍላጎት ይሁን» ይላል።

"tend the flock of God that is in your charge, exercising the oversight, not under compulsion but willingly, as God would have you do it- not for sordid gain but eagerly. Do not lord it over those in your charge, but be examples to the flock." [NRSV].

ስለሆነም መጋቢነት/ፓስተር ማለት የሚመግብ፥ እንደ እረኛ የሚያበላና የሚንከባከብ ማለት ነው። ዋና ተግባሩ ግን የሚሰብካቸውን ሰዎች ማንነት ማለትም መንጋውን በውል ለይቶ ማወቅ ነው። ይሁን እንጂ በሉቃስ ወንጌል ቀደም ሲል የጠቀስነውን ዓይነት መጋቢ አያመለክትም። ይህ በጎችን እንደ መመገብ፥ መንከባከብና መጠበቅን ያስገነዝባል። ሆኖም ግን «ግድ ሆኖብኝ ነው እንጂ፥ ተገድጄ ነው እንጂ፥ ሽማግልናም ይሁን ፓስተርነት ከብዶኛል፥ አልፈልገውም

ነበር፥ ወዘተ...» ካልን ጊዜ ሳያልፍብን ቦታ ብንለቅ ይሻላል። በግድ እግዚአብሔርን ማገልገል የተነቀፈ መሥዋዕት እንደማቅረብ ነውና። በአጭር ትርጉሙ ለመንጎች የሚጠነቀቅና የሚያስፈልጋቸውን የሚያቀርብ እረኛ ማለት ይሆናል።

እግዚአብሔር አምላክ ሙሴን እንዲህ ብሎት ነበር፤ *«ምግዚት የሚጠባውን ልጅ እንድታቅፍ በብብትህ እቀፋቸው----»* (ዘኍልቁ 11፥12 ይመልከቱ)። ሙሴ ሸክሙ ቢበዛበትም አምላካዊ መልስ ግን ተሸክማቸው ነበር። መልካም እረኛ በሕዝቡ ላይ አደጋና ቁጣ እንዳይመጣ በእግዚአብሔር ፊት የሚወድቅ ነው፤ የሚታየውም የእግዚአብሔር የክብር ጸዳል እንጂ ወንበር ወይንም ሥልጣን አይደለም። ከሕዝቤ በፊት እኔን ይላል። (ዘኍልቁ 14፥11-19 እና 16፥21ን ይመልከቱ)።

ይህንን ሁኔታ የሚገልጽ አንድ አጋጣሚ አስታውሳለሁ። በልጅነቴ አባቴ ሲሞት እኔም በጣም ታምሜ ነበር። አባቴ በጣም ጥሩ ሰው ስለነበር ሌሎቹ «ይህ ገፊ ልጅ ነው በሞተ» ሲሉ፥ አባቴ ግን የስለት ልጁ ስለነበርኩ «ከልጄ በፊት እኔን ይል ነበር» ብላ እናቴ ትነግረኝ ነበር። እንዳለውም ቀድሞኝ ሞተ። ሙሴም ይህን ነበር ያደረገው። ለሕዝቡ ሲግልድ፥ ስለ እነርሱ ብዙ ሲገደው ከርሞ፥ ዮርዳኖስን ሳይሻገር ወደ ፈስጋ ራስ ወጥቶ በሩቅ ተመልከቷት ተስፋይቱ ምድር ሳይገባ በናፍቆት ተሰናብቷል። በአንጻሩም የእግዚአብሔር ሕዝብ መሪ ራሱን መመርመር ይገባዋል። እግዚአብሔር በውሳኔው ጽኑ ነው። ስለዚህ ነበር ሙሴ ደጋግሞ ስለ መሻገሩ ጉዳይ ሲጠይቀው በዚህ ነገር ደግመህ አትናገረኝ፤ ይበቃሃል፤ አትሻገርም ብሎ የማለው። (ዘዳግም 3፥ 26-27 እና 4፥21ን ይመልከቱ)።

መልካም እረኛ ለበጎቹ እጅግ በጣም ይራራል፤ ይጠነቀቃልም። ሲርባቸውና ሲጠማቸው ያውቃል። ምን ጊዜ መሰማራት እንዳለባቸው፥ ወደ ሜዳ ተሰማርተውም ምን ጊዜ ወደ ቤታቸው መመለስ እንዳለባቸው ጠንቅቆ ይረዳል። ትክክለኛ እረኛ ያልሆነ ሞያተኛ ግን ማድረግ ያለበትን በውል ስለማያውቅ ሁልጊዜ ችግር ፈጣሪ ነው። ለራሱም ከባድ ወቅት ይሆንበታል።

የከተማ እረኛ ብዙም የሚያውቀው ነገር ባለመኖሩ በጎቹ «የሰው ስጥ» እየበሉ፥ የሌላ ሰው አጥር ሥር እየሄዱ አትክልት እያበላሹ ሲደበደቡ በዓይኔ አይቻለሁ። እርጉዝ የነበረች ተደብድባ የሞተች የአንዲት ምስኪን ሴትዮ በግን አውቃለሁ። እኔም በግሌ በቅርቡ አትክልት ሲበሉ በጎችን ደብድቤያለሁ። በኋላ ግን በጣም አሳዘኑኝ።

እነርሱ ምን ያድረጉ? ያስደበደባቸው እረኛው ነው። በተገቢው ስፍራ ስላላሰማራቸው ለችግር አጋለጣቸው። እንደዚያ ያለ እረኛ አልፎ አልፎ እርሱ ራሱም ከመደብደብ አያመልጥም። እረኛ ጨዋታና ቸልታ ሲያበዛ ውጤቱ ይኼው ነው። በቤተ ክርስቲያንስ እንዴት ይሆን? ለእረኝነቱማ በአገራችን እረኞች እየተቀጠሩ መንጋ ሲጠብቁ አይተናል። አንዳንዶቹ ያጋቱ ላሞችን እያለቡ ወተታቸውን ይጠጣሉ ይባላል።

መልካም እረኛ ግን በጎቹን ማሰማራት ያውቃል። አደጋ እንዳይደርስባቸው ይጠነቀቃል፤ ወደ አደገኛ ስፍራም እንዳይሄዱ ይጠብቃል። በገጠርም ቢሆን ቡቃያ ከበሉ «በአፈላማ» ይታሠራሉ። ከዚያም ባለ ንብረቱ በሽማግሌዎች የተጣለበትን ተመን ሳይከፍል መንጋውን ማስለቀቅ አይችልም። ያም እረኛ የማታ ማታ ወዮለት! ምን እንደሚገጥመው መገመት አያዳግትም። በመሠረቱ እረኝነት ቀላል ተግባር አይደለም። እረኛ የሚባለውም በጎቹን እስከጠበቀ ድረስ ነው። እረኝነት በመሠረቱ ሲታይ የሚከበርና የሚወደድ ሙያም አይመስለኝም። የከብት ጅራት ተከትሎ መሄድ ራሱ ከብት የሚያደርግ ያስመስላል። ይህንን ተግባር የሚወዱት ምናልባት ዘላኖች ብቻ ይሆናሉ። ይህ ተግባር ቀላል አይደለም። ፓስተር ፓስተር መባል ማዕረግ (Title or Position) ብቻ ከሆነ ወዮልን!

ለአንዳንዶች እንደሚመስል እሁድ መድረክ ላይ መቆምና መስበክ ብቻ አይደለምና። ለሕፃናት ልጆች መጸለይ፥ ማጥመቅ፥ የቀብርና የጋብቻ ሥርዓት ማስፈጸምና ሲታመሙ ሰዎችን ሆስፒታል ሄዶ መጠየቅ በሠለጠኑት ዓለም ያሉ ፓስተሮች የሚያከናውኑት ሙያ ሆኗል። በዚህ ሁኔታ ከሕያዋን ጋር ላይገናኝ የሞቱትን ቀባሪና ተስፋ የሌላቸውን አጽናኝ «ሐኪም» ዓይነት ይሆንና ያርፈዋል። እኛም ምኞታችን ይህ ከሆነ ወንጌል ተሸብቦ፥ በአንድ ካፒቴን ብቻ የሚንቀሳቀስ መርከብ ሆኖ መቅረቱ ነው ብዬ እሰጋለሁ። ከታሪክ እንደምናገኘው የፓስተሮች ብዛት ለውጥ ቢያመጣ ኖሮ እንደ ጃፓንና ሌሎችም በምዕራባውያን አገር ያሉ የቤተ ክርስቲያን ሕንፃዎች ባዶ ቸውን ባልቀሩ ነበር።

አንድ ጊዜ ዶ/ር ማክስ ዌል የሦስት ሰው ፓስተር ሆነው ነበር። ያውም አንደኛዋ ባለቤታቸው ነበረች። በኋላ ግን ሌሎችን በማሠልጠንና በማስተማር፥ ሌሎች ምእመናንን በማሳተፍ ትልቅ ቤተ ክርስቲያን ሊያደርጓት ችለዋል። ስለሆነም ነው የምእመናን መጠነ ሰፊ ተሳትፎ የሌለበት ቤተ ክርስቲያን ለውድቀት የሚዳረገው። ሁሉም ኃላፊነቱን አውቆ በሚገባ ቢንቀሳቀስ ገደቡ የሰማይ ጥግ ብቻ ይሆናል።

ለምሳሌ፡– በእስራኤል ምድር/በመካከለኛው ምሥራቅ ያሉ እረኞች መንጋውን ከኋላ ሳይሆን ፊት ለፊት እየሄዱ የሚመሩ ናቸው ይባላል። በጎቹም እረኛውን መስማት፥ መታዘዝና በመገዛት መከተል ይገባቸዋል። እረኛውም በጎቹን ይወዳል። ይህንንም ከዳዊት ሕይወት መማር ይቻላል። እንደተባለ «---በጎቹም ድምፁን ያውቃሉና ይከተሉታል።» (ዮሐንስ 10፡4ን ይመልከቱ)። በራሳቸው ፈቃድ እየሄዱ የሚባዝኑ በጎች ግን በአውሬ መበላታቸው አይቀሬ ይሆናል።

በተለይ በጎችን ከሰዎች ጋር በማዛመድ ካየናቸው ቢያንስ ሦስት ዓይነት ይኖራሉ።

<u>አንደኛ</u>፥ የሚፈሩ በጎች፡– እነዚህ ከሌሎች በጎች ጋር የማይደባለቁና ብቸኞች ሲሆኑ ጉዳትም ይደርስባቸዋል። ጉዳት ሲደርስባቸውም በቀላሉ ላይታወቅ ይችላል። ሁልጊዜ ይታመማሉ፥ እንደ ጤነኞች መቀላቀል አይሆንላቸውም፤ አጎንብሰው ይሄዳሉ።

<u>ሁለተኛ</u>፥ ያልተለወጡ/አጥፊ የሆኑ የይሁዳ በጎች፡–አታላዮችና አስመሳይ የሆኑ ሰዎች ባሕሪያቸውን ይጋሯቸዋል። ሌሎቹንም ወደ እርድ ይመራሉ፤ ወይንም በተኩላ ያስበላሉ። አውቀው አጥፊዎችም ናቸው።

<u>ሦስተኛ</u>፥ የሚባዝኑ/ዘላን የሆኑ በጎች፡– እነዚህ ደግሞ ባሉበት ደረጃ የማይረኩ ስለሆኑ ምግብ እያማረጡ ይዞራሉ። ከቤተ ክርስቲያን ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚዞሩ ምእመናን በእነዚህ ይመሰላሉ። ራሳቸው የሚፈልጉት ነገር ብቻ እንዲደረግላቸው ይመኛሉ፥ በዚህም ለእረኛው አይገዙም፥ አስቸጋሪዎችም ናቸው። በአጥር ሾልከው እንደሚወጡና እንደሚጠፉ በጎች ማለት ናቸው። እረኛውም ሁልጊዜ እነርሱን የሚያሳድድና የሚከታተል ከሆነ ሌሎቹ በጎች የሚመለከታቸው ያጡና ይጎዳሉ። አንድ ጊዜ አንድ የሀገራችን ሰባኪ (አባባ ኪዳም ይመስሉኛል) የዘመኑ ክርስቲያኖች ዘላን ሆነዋል እንዳሉት ማለት ነው።

በእስራኤል አገር ያሉ እረኞች መንጋውን ይመሩታል እንጂ እንደ እኛ አገር እረኛ ከኋላው ሆነው የሚገርፉት አይደሉም ይባላል። መቼም የእኛ አገር እረኞች እነርሱም ከሌሎች የተማሩት መግረፍ ስለሆነ ወይም ተገርፈው ስላደጉ ሁሌ ካልገረፉ አይሆንላቸውም። ለእርድ ሲወስዱቸው እንኳን ይገርፉአቸዋል። ተጭና የምትሄድንና ተሸክማ የምታበላቸውን አህያ ሲገርፉ፥ በእርሻ ወቅትስ ከመሬት ጋር ሲታገል የሚውልን በሬ በጅራፍ የሚገርፉ ስንቶች ናቸው? በዋሉልንስ ውለታ ወሮታቸው መመታት መሆን ይገባው ነበር? ከዚህ ብዙ ልንማር በተገባን ነበር።

ዊሊያም ኖብ እንደሚሉት፡-

> *"Biblical elders equip believers for the work of ministry (Ephesians 4:11-12). Pastors (or elders) are to develop and prepare believers through teaching, exhorting, directing, protecting, caring and serving the body of Christ." [Source:- Internet:In Depth Studies: 1998].*

ትርጉሙም «መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሽማግሌዎች አማኞችን ለአገልግሎት ማዘጋጀትና ማብቃት አለባቸው። (ኤፌሶን 4፥11-12ን ይመልከቱ)። ፓስተሮች/ሽማግሌዎች የክርስቶስ አካል የሆነውን ምእመን በማስተማር፥ በመምከር፥ በመምራት፥ በመጠበቅ፥ በመንከባከብና በአገልግሎት ማነልበትና ማዘጋጀት ይኖርባቸዋል።» በዚህም ሁኔታ ሁሉም ሽማግሌዎች ፓስተሮች ሁሉም ፓስተሮች ሽማግሌዎች ናቸው ይላሉ።

ፓስተርነት እኮ ቤተ ክርስቲያንን ማስተዳደር አይደለም ጥሪው፥ መንጋውን የመንከባከብና የመመገብ እንጂ። ያንንማ የአገዛዝ ስጦታ ላላቸው መተው ይሻላል። የፓስተርነት ጥሪ አለኝ የሚል ሁሉ የአገዛዝም ጥሪ አለው፥ አውቶማቲክ ነው ማለት ግን አይቻልም። ምን ነው መንጋውን ከመጠበቅና ከመንከባከብ ያኛው ያጓጓናል? ለመሆኑ ለመንጋው ልብ የሌለው ሰው እንዴት ሆኖ እረኛ/ፓስተር ይሆናል? ስለ ምንስ ፍርድ በራሱ ላይ ያመጣል? ያን ነበር ወይ ጌታ ያስተማረው? በጣም የገደደውስ ያ ነበር ወይ? ጌታ የሞተው ለሰውዬው ነው እንጂ ለአስተዳደሩ ሥርዓት አይደለም።

ደግሞም እንደሚባለው፡-

> *"Since all elders are pastors and all pastors are elders, the idea of an elder board with a 'pastor' as the Commanding Officer is without New Testament warrant." [Inetrnet: p.3].*

በመሆኑም «ሁሉም ሽማግሌዎች ፓስተሮች እና ሁሉም ፓስተሮች ሽማግሌዎች በመሆናቸው፥ በሽማግሌዎች ቦርድ ውስጥ ፓስተሩ እንደ መርከብ መሪ መኮንን የመሆኑ ጉዳይ የአዲስ ኪዳን ድጋፍ የሌለውና የማይታወቅ ልምምድ ነው» ማለት ነው።

ሽምግልና ፓስተርነት ወይም መጋቢነት ማለትም እረኝነት ነው። መጋቢነትም እንደ ሽምግልና ነው። ፓስተሩም ሽማግሌውም ሁለቱም የክህነት አገልግሎት አላቸው። እነርሱም ብቻ አይደለም ምእመኑም የእግዚአብሔር ካህን ነው። እረኝነት መቼም ዝቅተኛ የሥራ መስክና የአገልጋይ ተግባር መሆኑን ቀደም ብዬ ጠቅሻለሁ።

በአሁኑ ወቅት በቤተ ክርስቲያን የሚጋደሉለት፥ የሚጓጉለትና የሚፎካሙት ሥልጣን እየሆነ ነው። በመሠረቱ የፓስተርነት ጥሪ እኮ ቤተ ክርስቲያን ማስተዳደር አይደለም። ማስተዳደርም በራሱ ጥሪ ነው። ይህም ስጦታ ለቤተ ክርስቲያን ተሰጥቷል። እንደሚባለው «የፓስተርነት ሙያ» በአሜሪካን አገር የሚያስከብርና ጠቀም ያለ ደመወዝም የሚያስከፍል ነው።

አንድ እ. ኤ. አ. በ1996 ዓ. ም. በፓስተሮች አማካይ የወር ደመወዝ ላይ የተደረገ ጥናት እንደሚያስረዳው ከብር 35,512 በላይ እንደሚደርስ ነው። ይህም የወር ቀለብን፥ የተሽከርካሪና የቤት አበልን እንዲሁም የጤናና የጡረታ መዋጮን ጨምሮ ነው። እንደዚህም ሆኖ የአንድ ፓስተር በአንድ ቤተ ክርስቲያን ተወስኖ መቀመጥ በአማካይ ከሁለት ዓመት አይበልጥም ይባላል።

በሌላ በኩል ደግሞ ተመራማሪው ጆርጅ ባርና እንደሚለው በአሜሪካን አገር ውስጥ ካሉ ፓስተሮች የአመራር ስጦታ ጥሪያችን ነው የሚሉት በጣም ጥቂቶች እንዲያውም [5%] ብቻ እንደሆኑ ይናገራል። *[Anderson, 1999: P.37]* በዘመናችን ግን የሚፈለግ «የሙያ ዘርፍም» እየሆነ መጥቷል። በተለይ መንግሥትም የሥራ ግብር ስለማያስከፍል ተግባሩን እንደ ጥሪ ሳይሆን እንደ ሙያ ለሚመለከተው እጅግ ተፈላጊና ጠቃሚም ነው።

በአሜሪካን አገር እንደሚባለው «በአሁኑ ጊዜ ከአሜሪካን አገር ፕሬዚዳንት ቀጥሎ ሦስቱ ከባድ/አስቸጋሪ ተግባሮች ናቸው የሚባሉት የትልቅ ዩኒቨርስቲ ፕሬዚዳንት መሆን፥ የትልቅ ሆስፒታል አስተዳዳሪ መሆንና የትልቅ ቤተ ክርስቲያን ፓስተር መሆን ናቸው»[*] ይባላል።

በእርግጥ እንደ አሜሪካንና ጃፓን ባሉ አገሮች ፓስተሮቹ በምንዳ/በደመወዝ የሚተዳደሩ ናቸው። ስለ ጃፓን ባለ ቀለብ ተከፋይ የቤተ ክርስቲያን ሠራተኞች ኒየል ብራውን እንዲህ ጽፎአል፥ *"It is*

---

[*] Leith, Anderson, *"Leadership That Works"*, (Bethany House Pub., USA, 1999) P.25.

likely that Japan has a high ratio of Clergy to churches than any other country in the world." [Braun, 1971: P.34]. ምናልባት ጃፓን በዓለም ካሉት ሌሎች አገሮች ይልቅ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው የሠለጠኑ ባለ ቀለብ አገልጋዮች /የሙሉ ጊዜ አገልጋዮች ይኖራት ይሆናል ማለቱ ነው። ይህም የሆነው ጃፓን አገሪቱ በሥልጣኔ መጥቃ በአሁኑ ጊዜ 3/4ኛ የሚሆነው ሕዝቧ ከተማ ነዋሪ ነው ይባላል። ሆኖም ይህ ጃፓኖችን ለቤተ ክርስቲያን ዕድገት ምንም ያህል አልጠቀማቸውም። የዚህ ዓይነት ልምምድ ምእመኑ በወንጌል ስርጭት የሚኖረውን ተሳትፎ ስለሚገድበው አመርቂ ውጤት አላስገኘም ይባላል። ለዚህ ነው በሠለጠኑት አገሮች ያሉ አብያተ ክርስቲያናት የአባላት ዕድገት እየቀጨጨ የሚሄደው ይባላል።

በመሠረቱ ይህ የሙሉ ጊዜ አገልግሎት/ሙያ ቢፈለግም በቅጥር ስለሆነ ተግባራቸውን የሚያከናውኑት የሚፈጥሩት ችግር ሥር ሳይሰድ በቀላሉ ሊወገድ ይችላል። እንደ አፍሪካ አገር ፓስተሩ በር ቆልፎ አይጠፋም። አንድ ጊዜ በታንዛኒያ ይሁን በዛምቢያ ነባሩ መጋቢ ለወጣት ፓስተሩ እንዲለቅ ሲጠየቅ የቤተ ክርስቲያኗን ሕንፃ በር ቆልፎ መጥፋቱን ከጋዜጣ አንብቤአለሁ። እዚህም ይከሰት ይሆንን? እግዚአብሔር ይጠብቀን!

እንደ እውነቱ ከሆነ ቀደም ሲል እንደ ተጠቀሰው ይህ ፓስተር የሚለው ቃል በአዲስ ኪዳን ውስጥ አንድ ጊዜ፥ ያም እንኳን ቢሆን በኤፌሶን 4፡11 ውስጥ ብቻ የሚገኘው ነው። በብሉይ ኪዳን ግን በአያሌ ስፍራዎች እንደ እረኛ *(Shepherd)* ተጠቅሶ ይገኛል። እነዚያም በሕዝቡ የተመረጡ ሽማግሌዎች እንጂ መጋቢነት በስጦታ እንደምንለው በኤፌሶን 4፥11 ውስጥ እንዳለው ዓይነት አይደለም። በግሪኩ ትርጉምም ቢሆን «ፖይሜን» የሚለው ቃል ያለ ልዩነት እንደ እረኛም እንደ ፓስተርም ሊቆጠር ይችላል ይባላል። ይህ ምንም ችግር የለውም። በመሆኑም የመጋቢዎች ሙያ የሽማግሌዎችም ነውና።

መልካም እረኛ ለበጎቹ ይሞታል። አላዳሪው/ጌታው ስለሚቆጣው ብቻ ሳይሆን ስለሚያዝንላቸውና በጎቹንም ስለሚወዳቸው ለጠላት አሳልፎ አይሰጣቸውም፤ አውሬ ሲመጣም አውላላ ሜዳ ላይ ትቷቸው አይሸሽም። የእሴይ ልጅ ዳዊት በእረኝነቱ ዘመን ያደርግ የነበረው ይህንኑ ነበር። ከቀበሮ ሳይሆን ከአንበሳና ከድብ ታግሏል። ከዚያም በጥቂቱ የታመነው እረኛ በመፈንቅለ መንግሥት ሳይሆን በእግዚአብሔር ምርጫ ወደ ቤተ መንግሥት ተንቀሳቅሶ ለንግሥና በቅቷል። ትክክለኛ ትርጉሙም ሌላ ልብ ወለድ ሊደረትበት ካልታሰበ ይኼው ነው።

ለምሳሌ፡- ስለ እረኛ የተጠቀሱ ጥቂት ጥቅሶችን በማቴዎስ 9፥36፤ 26፥31፤ ማርቆስ 6፥34፤ ሉቃስ 2፥8፥ 15 እና 20፤ ዮሐንስ ወንጌል 10፥2 እና 12፤ ዕብራውያን 13፥20 እና 1ኛ ጴጥሮስ 2፥25ን ይመልከቱ።

በአጠቃላይ መልካም እረኛ፡-

1. እግዚአብሔርን በትክክል የሚያውቅና እርሱም በእግዚአብሔር የሚታወቅ ነው። መልካም እረኛ ለብርድ ደበሎ፥ ለውኃ ጥም ኮዳ፥ ለዝናብ ገሣ እየተሸከመ የሚመላለስ እንጂ በጎቹን ትቶ የሚሸሽ አይደለም። መልካም እረኛ ለሥጋው ሞቶ ለነፍሱ ያደረ ነው። እውነተኛ ለውጥ ያለው የሥጋውን ፍላጎት የማያዳምጥ ነው። (ገላትያ 5፥16-26ን ይመልከቱ)። ሁል ጊዜ ራሱን ሳይሆን የበጎቹን ባለቤት ለማስደሰት ይሠራል። «እንዲሁ እናንተ ደግሞ የታዘዛችሁትን ሁሉ ባደረጋችሁ ጊዜ፥ የማንጠቅም ባሪያዎች ነን፥ ልናደርገው የሚገባንን አድርገናል በሉ» (ሉቃስ 17፥10ን ይመልከቱ)።

ጳውሎስ እንዳለው «ነገር ግን ወንጌልን አደራ ይሰጠን ዘንድ እግዚአብሔር የታመንን ሆነን እንዳገኘን መጠን፥ እንዲሁ እንናገራለን፥ ልባችንን የሚመረምር እግዚአብሔርን እንጂ ሰውን ደስ እንደምናሰኝ አይደለም። እንደምታውቁት፥ እያቆላመጥን ከቶ አልተናገርንም፥ እግዚአብሔርም እንደሚመሰክር እያመካኘን በመሳምጀት አልሠራንም።» (1ኛ ተሰሎንቄ 2፥4-5 ይመልከቱ)። እረኛው በጎቹ ሲወፍሩና ተስማምቷቸው ሲያይ ከእነርሱም ሊጠቀም ሲያስብ/ሲከጅል መስመር መሳቱ ነው። በጎቹ የባለንብረቱ ናቸውና።

እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፥ «---እናንተም በጎቼ፥ የማሰማርያዬ በጎች፥ ሰዎች ናችሁ እኔም አምላካችሁ ነኝ።» (ሕዝቅኤል 34፥31 ይመልከቱ)። በሌላ ቦታ በሕዝቅኤል 34፥2-6 ውስጥ እንደዚህ ይላል፥

«---ራሳቸውን ለሚያሰማሩ ለእስራኤል እረኞች ወዮላቸው፥ እረኞች በጎችን ያሰማሩ ዘንድ አይገባቸውምን? ጮማውን ትበላላችሁ፥ ጠጉሩንም ትለብሳላችሁ፥ የወፈሩትን ታርዳላችሁ፥ በጎቹን ግን አታሰማሩም። የደከመውን አላጸናችሁትም፥ የታመመውንም አላከማችሁትም፥ የተሰበረውንም አልጠገናችሁትም፥... በኃይልና በጭቆና ገዝታችኋቸው። እረኛንም በማጣት ተበተኑ፥ ለምድርም አራዊት ሁሉ መብል ሆኑ፥

ተበተኑም። በጎቼ በተራሮች ሁሉና በረዘሙ ኮረብቶች ሁሉ ላይ ተቅበዝብዘዋል፡ በጎቼም በምድር ፊት ሁሉ ላይ ተበትነዋል፡ የሚሻም የሚፈልግም አልነበረም» ብሎ አስቀድሞ የተተነበየው እንዳይደርስብን ልንጠነቀቅ እንደሚገባ እገምታለሁ። እረኞች የወፈሩትንና ጠቃሚ ገቢ የሚያስገኙትን ብቻ ሳይሆን ከሲታዎችንም መንከባከብና መጠበቅ ያስፈልጋቸዋል። ያም ተግባራቸው ነው።

2. መለኮታዊ ጥሪ ያለው ነው። እረኛ የሆነው ከግል ስሜቱ በመነጨ ፍላጎትና ምኞት ወይም ከአጋጣሚዎች ቅንብር የሚነሣ አይደለም። እረኝነቱ ከሥነ መለኮት ትምህርት ቤት የተሰጠው ብቃት ሳይሆን በመለኮታዊ ጥሪ ቀንበር የተጫነበት ወይም እግዚአብሔር ኃላፊነትን የጣለበት/ባላደራ ሰው ማለት ይሆናል። ማስተማር መቻሉ ብቻ እረኛ አያደርገውም። የእረኝነት ጥሩ ጥበብ ስላለው ሳይሆን ለበጎች ግድ የሚል ልብ አለው። ሽከም ይሰማዋል፤ ሲርባቸው ይርበዋል፤ ሲጠማቸውም ይጠማዋል። ወዴት መመሰግ እንዳለባቸው አስቀድሞ ያስባል እንጂ ጭንጫ መሬት ላይ አያሰማቸውም። እንዲህ ያለ ሰው ከከበሬታ ይልቅ ውርደት፥ ከወንበር ይልቅ መደብ መቀመጫን መርጦ የተቀበለ ነው።

እግዚአብሔር ይህንን ስጦታ ሊሰጥ እንደሚችልና እንደ ሰጠ በሮሜ 11፥29፤ በ1ኛ ቆሮንቶስ 12፥28፤ እና በኤፌሶን 4፥11 ውስጥ ሲጠቀስ፥ ያለ እርሱ እርዳታ የሚቻል ተግባር አይደለም። እንደው በጉልበት እረኛ ልሁን ቢባል በጎቹን ደብድቦ ወይም ራሱ በበጎቹ ተወግቶ ይሞታል። አልፎ አልፎ የሚታየው ትርምስም ምናልባት ከዚህ ዓይነት ሁኔታ የመነጭ ሊሆን ይችላል። በመንፈሳዊ ትርጉሙ እረኝነት የተቀደሰ አሳብ ያለው ነው። ሙሴ ለእስራኤል ሕዝብ የሕግ መሰጠትን እንዳመጣ ጌታ ኢየሱስም ወደ ላይ ከፍ ሲል ስጦታን ለሕዝቡ ሰጥቷል። የተሰጠውም ስጦታ የክርስቶስ አካል ማለትም ቅዱሳን በአገልግሎት በሚገባ ተሰማርተው እንዲሠሩ ነው። ይህም የቢሮ ሥልጣን አይደለም። የቢሮ ሥልጣን ይሻራል፤ ጸጋ ግን ዘወትር በሁሉ ይጸናል። ስጦታውም የቢሮውን ተግባር (Function) እንጂ የተሰጪውን የቢሮ ሥልጣን አያመለክትም። በመሆኑም ብዙ ትግል አያስፈልገውም።

ስለዚህ እውነተኛ እረኛ የክርስቶስን ፍቅር ተገንዝቦ ስለ መንጋው በጎ የሚያስብ ሲሆን ግድ የሚለውም የመንጋው በትክክል መሠማራት እንጂ የእርሱ ስንቅ መሰነቅ ወይም የሚመቸው ቦታ መቀመጥ አይደለም። (2ኛ ቆሮንቶስ 5፥14ን ይመልከቱ)። ከዚህም ሁሉ በላይ እንደ ካሌብ እግዚአብሔርን ፈጽሞ የተከተለ ሰው ነው ማለት ይቻላል። (ኢያሱ 14፥8ን ይመልከቱ)።

3. ለራሱ የማይኖር ነው። የውጭ ሰውነቱ ቢጠፋም የውስጥ ሰውነቱ የሚታደስና የሚለመልም ነው። በጎቹ ቢያሰለቹትም የማይታክትና በድካማቸው የማይሳለቅ ነው። ዘወትር የሚማልድላቸው ነው። የበጎቹ ባለቤት ለእረኛው እንደሚጠነቀቅ ስለሚገባው ለበጎቹ ኖሮ ያልፋል (ሻማ ለሌሎች ብርሃን እየሰጠ ራሱ ግን እየተቀጣጠለ ቀልጦ እንደሚያልቅ ማለት ይቻላል)። (2ኛ ቆሮንቶስ 4፥16፤ 5፥15 እና ኤፌሶን 3፥13ን ይመልከቱ)።

4. ከመንጋው የሚተዋወቅና የቅርብ ረዳታቸውም ነው። በጎቹ ድምፁን የሚሰሙት፥ ሰምተውም የሚሸሹት ሳይሆን የሚከተሉት ምንኛ የታደለ እረኛ ነው? እንስሳት ብዙ አያውቁም እንላለን። ግን አሳምረው ያውቃሉ። ፍቅር ይገባቸዋል። እንኳንስ እንስሳት ተክሎችም ያውቃሉ ይባላል። (ዮሐንስ ወንጌል 20፥27–35፤ ኤፌሶን 1፥15–16 እና 1ኛ ተሰሎንቄ 2፥9–12ን ይመልከቱ)።

5. መልካም ምሳሌ ሊሆን የሚችል ነው። በጎቹን የሚመራ እንጂ ከኋላ ሆኖ የማይነዳ፥ የሚመግብ እንጂ ጥፋት የማያመጣባቸው፥ በረሃብ የማያሠቃያቸው፥ የሚናገረውን የሚያደርግና ፍቅሩ በተግባር የሚገለጽ ነው። (ኤርምያስ 17፥16፥ 1ኛ ጢሞቴዎስ 3፥1–13፤ 2ኛ ጢሞቴዎስ 1፥13–14፤ 2፥15 እና 1ኛ ጴጥሮስ 5፥3 ይመልከቱ)።

6. መንጋውን ወደ ተሻለ ስፍራ የሚያደርስ ነው። ይህ እረኛ ራእይ ያለው ሆኖ ሕልሙን ብቻ ለመተርጎም ያልተነሣ

ወይም በተውሶ ራእይ የማይኖር፥ በእግዚአብሔር አሸናፊነት የሚታመንና መንጋውን ወደ ተሻለ መስክ የሚያሰማራ/በለመለመ መስክ የሚያሳድር ድፍረትና እምነት ያልተለየው ነው። የሌሎች መሪዎችን ልብ የሚያሳርፍ ሆኖ በየዕለቱ ከመንጋው ባለቤት መመሪያ እየተቀበለ መንጋውን ለመጎብኘት የተዘጋጀ ሰው ነው። የመንጋው ባለቤት በጎቹን በባለ አደራነት ቢሰጥም ሁኔታዎችን በቅርብ ይከታተላል።

እውነተኛ መጋቢ ከዚህ በላይ የተጠቀሱትንና ሌሎችንም መስፈርቶች ሊያሟላ የግድ ነው። አገልግሎቱ ኃላፊነት መሸከምን ስለሚያመለክት በቀላሉ የሚታይ አለመሆኑን ማስገንዘብ ይበጃል። በዚህም መሠረት መልካም እረኛ ማንነቱን ሊመዝን ይችላል። ይህ መሪ ድካም የሌለበት ፍጹም ሰው ነው ማለት ግን አይደለም። በድካሙም ግን ቅንነት ከታከለበት ባለቤቱ ይረዳዋል። ይህም ከስጦታዎች ቁንጮ ሳይሆን ከስጦታዎች አንዱ ነው– አይበልጥም፥ አያንስም።

3.2 ሽማግሌዎች/እረኞች፥ ኤጲስ ቆጶሳት

(Presbyteros,Bishop Overseers,Elders) :-

በመሠረቱ ሽማግሌዎች ከብሉይ ኪዳን ጀምረው በሕዝብ እየተመረጡ በሥልጣን የነበሩ ናቸው። ሽማግሌ ማለት በዕድሜ የገፋ ሰው ሲሆን በቤተ ክርስቲያን ግን በተለይም በአዲስ ኪዳን የዕድሜ ሁኔታ ሳይጠየቅ ብቁ ሆነው ለአገልግሎት የተሾሙትን ሰዎች ማለት ነው። ጌታችን ኢየሱስ በምድር በነበረበት ዘመን የአይሁድ ሽማግሌዎች ከካህናት አለቆች ጋር ሥልጣን ተጋርተው ሸንጎ ይመሩ እንደ ነበር ይታወቃል። (ማቴዎስ 15፥2፤ 16፥21–23፤ የሐዋርያት ሥራ 4፥5፥ 8 እና 23ን ይመልከቱ)።

በግዕዝም ቢሆን ካህን፥ ቀሲስ፥ ቀሳውስት ወዘተ... የሚለው ሽማግሌ እንደ ማለት ነው። በ1951 ዓ. ም. በታተመው የከሳቴ ብርሃን ተሰማ የአማርኛ መዝገበ ቃላት ሽማግሌ ማለት፥ ጥሬ ቃሉ «ዘር፥ ስም፥ ከጎልማሳነት አልፎ ትክክል እውቀት ያለው፥ አእምሮ የሚመዝን፥ ጨዋ ወይም የተጣላን ገላጋይ ወይም በዘመን የበለጠ ያረጀ፥ ያደገደገ፥ መነሣት መሄድ ያቃተው» ይለዋል። ይህም እንደ መጋቢው ትርጉም አካላዊ ተፈጥሮን እንጂ መንፈሳዊ ትርጉሙን አይሰጥም።

ዳሩ ግን ሽማግሌ የሚለው ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በግልጽ የታወቀ ሲሆን በአዲስ ኪዳን ብቻ በግሪኩ [Πρεσβυτεροσ = Presbyter, elder] የሚለው 18 ጊዜ ያህል ተጠቅሶ ይገኛል። በአጠቃላይ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ደግሞ ከ68 ጊዜ በላይ የተጠቀሰ ቃል ነው። ሽማግሌ እንደ ፓስተር የተጠቀሰበትና ፓስተር የሚለውም ቃል የታየበት በኤፌሶን 4፥11 ውስጥ ያለው ብቻ ነው። እርሱም ቢሆን ከማስተማር ጋር ነው፥

[Τουσ δε ποιμενασ και διδασκαλουσ = And some shepherds/ pastors and teachers] «...ሌሎቹም እረኞችና አስተማሪዎች እንዲሆኑ ሰጠ» ይላል።

ይህ ሽማግሌ የሚለው ቃል (ሁልጊዜ በብዙ ቁጥር ማለትም ሽማግሌዎች) በሰማያዊ ማዕረግ ውስጥ እንኳን ያለ በመሆኑ ብዙ ማቃለል ያለብን አይመስለኝም። ይህም «አፍቃሪ ሽማግሌነቴን» ለማሳየት ሳይሆን የምንጽፈውንና የምንናገረውን አስተውለን እንድናደርግ ብቻ ነው። (ራእይ 4፥4 እና 10፥ 5፥ 6፥ 8 ፥ 11፥ 14፤ 7፥11 እና 13፤ 11፥16፤ 14፥13 እና 19፥4) የተጠቀሰውን ለአብነት ያህል መመልከት ይበቃል። ብቁ ሽማግሌዎች ከሌሉ ባሕሪያቸው ነው እንጂ ሽምግልና እንደ አገልግሎት የተከበረና በእግዚአብሔርም የሚታወቅ ሹመት ነው።

ሐዋርያት በጊዜያቸው ሐዋርያም ሽማግሌዎችም ነበሩ። ሁሉም ሽማግሌዎች ግን የሚታወቀውን ያህል ሐዋርያት አልነበሩም። ጳውሎስ በፊልጵስዮስ 1፥1 ውስጥ እንደጠቀሰው ለቤተ ክርስቲያን ደብዳቤ ሲጽፍ «ከሽማግሌዎች (ኤጲስ ቆጶሳትና) ዲያቆናት ጋር በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት ቅዱሳን ሁሉ» ይል ነበር። ይህም በጥቂቱ እንደሚያመለክተው የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን ስብጥር ሲሆን ፓስተር፥ መጋቢ፥ እረኞች ብሎ ሌላ መደብ መፍጠር አላስፈለገውም። እንዲያውም አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ አዋቂዎች እንደሚሉት ሌላ የሥልጣን ተጋሪ ቢኖር ኖሮ በትክክል ሊጠቀስ ይችል እንደ ነበር ያረጋግጣሉ።

የቀድሞ አባቶች፥ (ለምሳሌ እነ ጀሮምና ካልቪን) የጠቀሷቸውን ነጥቦች በዚህ ስፍራ በግልጽ ማስቀመጥ ያስፈልግ ይሆናል።

"---and before parties had so multiplied under diabolic influence, the churches were governed by a council of elders."[1]

ትርጉሙም ፦«በዲያቢሎስ ተጽዕኖ ፓርቲዎች እንዳሁኑ ሳይስፋፉ/ሳይባዙ፥ አብያተ ክርስቲያናት የሚመሩት በሽማግሌዎች ጉባኤ ነበር» እንደ ማለት ነው።

ቀጥሎም በተሐድሶ እንቅስቃሴ ትልቅ ድርሻ የነበረው ካልቪን እንዲህ ብሏል፥

"In giving the name of bishops, presbyters, and pastors, indiscriminately to those who govern churches, I have done it on the authority of the scripture, which uses the words as synonymous."[2]

«ቤተ ክርስቲያናትን የሚመሩ ኤጲስ ቆጶሳት፥ ሽማግሌዎችና ፓስተሮች ብሎ ስያሜ ለመስጠት ቃላቶቹን ተመሳሳይ አድርጎ በሚያቀርባቸው በእግዚአብሔር ቃል ሥልጣን መሠረት አድርጌአለሁ» ብሏል።

ከነዚህም ቀደምት አባቶች ፍንጭ እንደምናገኘው በቤተ ክርስቲያን መሪዎች መካከል መለያየት እንደነበረም መረዳት ይቻላል። በዚህም መሠረት አንዱ ሌላውም ነው። እንደ አሁኑ ዘመን ቤተ ክርስቲያን የሥልጣን ጥመኞች አልገጠማትም ማለት ግን አይቻልም። ገና በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን እንኳን ሐዋርያው ጳውሎስ በፊልጵስዮስ 4፥2-3 የተጠቀሱት ሁለት ሴቶች፥ «ኤዎድያንና ሲንጤኬን» የተባሉትን በገጠማቸው የአንድነት ችግር እንዲስማሙ የምክር እገዛ ማስፈለጉን ጽፎአል። ምናልባትም እነዚህ ሴቶች በቤተ ክርስቲያን በመሪነት የታወቁ ሳይሆኑ እንደማይቀሩ እገምታለሁ። ይህ ጥል ታዲያ ጳውሎስን አሳስቦት ነበር። ባለመስማማታቸው ግን ብዙ ጉዳት ሳይደርስ እንዳልቀረ እገምታለሁ።

የእግዚአብሔርን መንጋ በሽምግልና ሹመት ማለትም መሪነት ተቀብለው የሚያገለግሉ ሰዎች የሚከተሉትን ሊያሟሉ ይጠበቅባቸዋል። ይህም በ(1ኛ ጢሞቴዎስ 3፥1-7 እና በቲቶ 1፥5-11 ከተጠቀሱት በተጨማሪ አስፈላጊ ናቸው ያልኳቸውን መስፈርቶች ሊያሟሉ እንደሚገባ ለመጠቃቃስ እሞክራለሁ።

በአጭሩ ለሽማግሌዎችም ምን ማድረግ እንዳለባቸው ለማስቀመጥ፦

1. መንጋውን መመገብ፥ በቅርብ መከታተል፥ በፍቅርና በውዴታ መግዛትና ማስተዳደር። (1ኛ ጴጥሮስ 5፥2-3ን ይመልከቱ)።

2. የእግዚአብሔርን መንጋ በበላይነት መምራት፥ መቆጣጠር፥ በአገባቡ በሥርዓት እንዲሄድ ማድረግ። (የሐዋርያት ሥራ 20፥28ን ይመልከቱ)።

3. መንጋውንና እግዚአብሔርን በውዴታ ማገልገል። «እንዲያው ሰው ስለጠፋ ነው እንጂ፥ ተለምኜ ነው እንጂ» ከማለት አለመቀበል ይበጃል። የማይሠሩ ከሆነ ኃላፊነትን ተቀብለው ችላ ቢሉ/ቢያዝረከርኩ ከእርግማን አያመልጡም።

4. የእግዚአብሔርን መንጋና ርስት በኃይል አለመግዛት። ለመንጋው አርአያ መሆን። (1ኛ ጴጥሮስ 5፥3)።

5. ለግል ጥቅም ፍለጋ ሽምግልናን አለመቀበል፥ ለሌሎችም ዕንቅፋት አለመሆንና በሥልጣን አለመመካት። (1ኛ ጴጥሮስ 5፥2፤ ቲቶ 1፥7ን ይመልከቱ)።

6. እጅ በመጫን ለበሽተኞች መጸለይና የጸጋ ስጦታዎችን ማነሣሣት፥ ማበረታታት። (1ኛ ጢሞቴዎስ 4፥14)።

ሽማግሌዎች እነዚህንና መሰል ተግባሮችን ማከናወን ግዴታቸው ሲሆን የተሰጣቸውና የሚሰጣቸው ኃላፊነት የምእመናን ወኪል መሆን ብቻ ሳይሆን የእግዚአብሔርንም ቤት በቅርብ መከታተልና መጠበቅ ነው። ሽማግሌዎች ግንባር ቀደሞች ሆነው አጠቃላይ የቤተ ክርስቲያንን አሠራር የሚከታተሉ ሊሆኑ ይገባል። በመሆኑም ሽክሙ ከሌላቸውና የመንጋው ነገር የማይገዳቸው መስሎ ሲሰማቸው ከመዘግየቱ በፊት ቶሎ ኃላፊነታቸውን ቢለቅቁ ይመረጣል። ሽምግልና የእግዚአብሔር ሕዝብ ባሪያ መሆን፥ አገልጋይ መሆን እንጂ የሥልጣን ሹመት እንዳልሆነ መገንዘብ ያስፈልጋል። ሽማግሌዎች በፖለቲካዊ አመራረጥ ሳይሆን በትክክለኛ ሽክምና የሕዝብ ፍላጎት ቦታ ከያዙ፥ በዚያች ቤተ ክርስቲያን እውነተኛው ሰላም ሊሰፍን ይችላል። ከሌሎች አገልጋዮችም ጋር መያያዝና መደጋገፍ ይኖራል።

ዳሩ ግን አንዳንድ ቦታ እንደሚደረገው «እሺ-እሺ ባዮች» (Yes-men) የዋሆች ሆነው ለምንም ሳይረቡ ይቀራሉ። እንዲያውም ለሌላው መጠቀሚያ ሲሆኑ የእግዚአብሔር ቤት ሥራ ይበላሻል። ከዚያም

ልቀቁ ከመጣ፥ ሞቼ እገኛለሁ ብለው ዘመቻ ይጀምራሉ። በዚህ መልኩ እንደ ፓስተሩ ሽማግሌውም «የሚያሳፍር የእግዚአብሔር ባሪያ» ሆኖ ይመላለሳል። (2ኛ ጢሞቴዎስ 2፥15ን ይመልከቱ)። ቀድሞ በአንድ አሳብ እንዳልተስማሙት እንደ ኤዎድያንና ሲንጤኪን መለያየት ይሰፍናል። (ፊልጵስዮስ 4፥2ን ይመልከቱ)። ሌሎች አገልጋዮችንም መግፋትና ቀንዳቸውን ማስረዘም ይመኛሉ። ሥልጣናቸውም ገደብ የሌለው ሆኖ የሙሉ ጊዜ አገልጋይ የሚባሉትን እንደ ግል አሽከር ለመቁጠር ይዳዳቸዋል። ይህን መሰል ተግባር የሚፈጽሙ ሁሉ ጊዜ ሳያልፍባቸው ለንስሐ ቢዘጋጁ ይበጃል። አገልግሎትንም በችሮታ ለማከፋፈል ሲሞክሩ ይታያሉ።

3.3. የሽማግሌዎች/የመጋቢያን ጥምር/የጋራ አስተዳደር፡-

(Plurality of Leadership)

በመሠረቱ ሽምግልና (Elder) እንደ መሪ/ኃላፊ፥ ኤጲስ ቆጶስ (Bishop, Overseer) የሚሠራውን ሥራ እንደ መግለጫ ሲሆን መጋቢ/እረኛ (Pastor, Shepherd) ደግሞ ተግባርን ያመለክታል ይባላል። በዚህ ስፍራ በአሁኑ ጊዜ በብዙ ቦታዎች እየተሠራበት ያለና የተሻለ አመራር ሊኖርበት ይችላል ተብሎ የሚታሰበው /በተለይም መጋቢው ከዕለት ዕለት ጥቃቅን ተግባራት ውስጥ ወጥቶ (ሁሉም በጋራ) በወል ይምሩ (Plurality of Leadership) የሚለው አስተሳሰብ ነው።

በተበተነውም መጠይቅ ውስጥ ለአሁኗ ኢትዮጵያ የቤተ ክርስቲያን አመራር የሚበጀው የቱ እንደሆነ ለቀረበው ምርጫ፥ [45.2%] የሚሆኑት ይህንን አሳብ ሲያመለክቱ፥ በሽማግሌዎች (Elders) ጉባኤ ብቻ መመራት ይበጃል ያሉት ደግሞ [28.6%] ናቸው። በፓስተር/ፓስተሮች መመራትን የደገፉት ሰዎች ቁጥር ግን [12%] ብቻ ሆኗል።

የሚያስገርመው [14.2%] የሚሆኑት መላሾች ግን «ከዚህ በፊት ተሞክሮ የማያውቅ» ዓይነት ቢኖርና ቢተገበር ይሻላል ያሉና ሁለቱንም ያልደገፉ ሆነው ተገኝተዋል። ይህ ቁጥር ትንሽ ባይሆንም፥ ሁለቱም ቡድኖች ትምህርት ሊያገኙበትና መስተካከል ያለበት ነገር መኖሩን ይጠቁማል። ቤተ ክርስቲያን በፓስተሮች ትመራ የሚለውን ጽንፍ ለሚያራምዱ ግን የሕዝቡ አስተያየት መርዶ ሊሆንባቸው

ይችላል። መጠይቁ ሲበተንም ሆን ተብሎ ይህንን አሳብ ያራምዳሉ ለሚባሉ ፓስተሮች ጭምር ተሰጥቶ ነበር። በአጠቃላይ አስተያየቶቻቸውን መስጠት ካልፈለጉ ከአንዳንዶች በስተቀር ሌሎች ሸክሙ የተሰማቸው መልሰዋል። ውጤቱም እንደዚህ በግልጽ እንደሚታየው ሊሆን ችሏል። ሕዝብ አያውቅም አይባልም፤ አሳምሮ ያውቃል። የመንገዶች አካሄድም ይሸተዋል።

ለነገሩ በዚህ ዓይነት የጋራ አመራር አንድነትና ጎብረት ከሌለ ውጤታማ መሆን አይቻልም። መሪዎች ራሳቸው እንደ ሁለት ቡድንና ካምፕ ከተያዩ ጥምር አስተዳደሩ በምንም መልኩ ቢሆን ሊሰምር አይችልም። ሁለት የፓርቲ ቡድን ሆኖ ይቀጥላል። እንደሚታወቀው በአፍሪካ ውስጥ አንድ ሰው ብቻ መሪ ማድረግ አምባገነንነትን ማስፈን ለመሆኑ ሳይታለም የተፈታ ነው። ይህን በብዙ መንገድ ለማስተባበል ብንሞክርም ሁልጊዜ ተግባር ይገልጠዋል። መሪ ማለት ገዢ መስሎ ስለሚታየን የሰው ልጅን ክቡርነትንና ዋጋውን/እሴቱን (Dignity & Value) ሳንረዳ ዘመን ያልፍብናል።

ቀበሮ እንዳለችው «ለሰው ሞት አነሰው» አይደለም። ሰው በአርአያ ሥላሴ የተፈጠረ፥ የሕያው የእግዚአብሔርም ልጅ ነፍሱን የከፈለለት ክቡር ፍጡር ነው። እግዚአብሔርም ለሰው ያለው ዓላማ እጅግ ትልቅ ነው። እንደ እውነቱ ከሆነ በመጨረሻው ጊዜ ብዙዎች ያልጠበቅናቸው ሰዎች መንግሥተ ሰማይ ገብተው የተጠበቁት እዚያ ላይኖሩ ይችላሉ። ያንን ልናውቅ ይገባል።

በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ደጋግሞ የሚነሣ የመሪነት ጥያቄ አለ። ቤተ ክርስቲያንን ፓስተር ይምራት ወይስ ሽማግሌዎች? በጋራ ሁሉም በአንድነት ይምሩ ወይስ ምን ይሻላል? አንድ ወገን ብቻ ይምራ ማለት ደግሞ አምባገነንነትን እንደሚያሰፍን ታይቷል፤ ይታያልም። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥስ የነበረው ልምምድ እንዴት ነበር? እነዚህ ጥያቄዎች ከዚህ በፊት በተገለጹት አሳቦች ስለተካተቱ እንደገና ማንሣት አስፈላጊ አይሆንም። ቢሆንም ለአብነት (የሐዋርያት ሥራ 15፥4፥ 12፥ 22፥ 23) የአንድነትና የጋራ አሠራርን ጠቋሚ ነበር። ለምሳሌ፦ በድሮው ትርጉም በቁጥር 4 ውስጥ፥ «---ቤተ ክርስቲያንና ሐዋርያት ሽማግሌዎች» የሚለው ትንሽ የተዛባ የአተረጓጎም ችግር ያለ ይመስላል። በአዲሱ ትርጉምና በእንግሊዘኛም ይሁን በግሪክ አንድ ዓይነት ናቸው። ይህም ቁጥር 4 በአዲሱ ትርጉም እንዲህ ይላል፥ «--- ቤተ ክርስቲያንና ሐዋርያት፥ ሽማግሌዎችም ተቀበሉአቸው» ሲል፥ በእንግሊዘኛም፥

"...they were welcomed by the church and the apostles and the elders". [UBS]. ይላል።

በግሪኩም፥

[Τησ εκκλησιασ και Των αποστολων και Των Πρεσβυτερων]

ጥርት አድርጎ የተለያዩ ሦስት አካላትን ያሳያል። በቁጥር 6ትም «ሐዋርያትና ሽማግሌዎችም---» የሚለው እንደ ሁለት ባለቤትነት ያለው አካል/ቡድን፥ [οι αποστολοι και οι πρεσβυτεροι] አድርጎ ያቀርበዋል።

በዚህ መልኩም ቁጥሮቹ አንድ በመሆናቸው የትርጉም ልዩነት አይታይባቸውም። የድሮው ትርጉም ግን ለያይቶ ማቅረቡ ተገቢ አይደለም ማለት ነው። «ያን ጊዜ ሐዋርያትና ሽማግሌዎች ከቤተ ክርስቲያኑ ሁሉ ጋር» ለመጨረሻ ውሳኔያቸው በጋራ ተባብረው እንደ ነበር በግልጽ ያሳያል። (ቁጥር 22-23ን ይመልከቱ)። የጋራ ጥምር አስተዳደር ማለትም ይኼው ነው። ሌላ ምንም ምሥጢር የለውም።

በመሆኑም መሪነት በዘመናት ውስጥ እያደገና እየተደራጀ የሄደ እንጂ፥ አንዳንዶች እጅግ መንፈሳዊ ለማድረግ እንደሚያስተምሩትና እንደሚጽፉት አለመሆኑን በግልጽ ማስቀመጥ ይቻላል። በአንደኛው ምእተ ዓመት የቤተ ክርስቲያን ታሪክ የሰከነ የቤተ ክርስቲያን የአመራር ተዋረድ ነበር ብሎ መናገር ፈጽሞ የሚቻል አይመስለኝም። በእርግጥ በወቅቱ ኃላፊነት የወደቀባቸው ሐዋርያት በስደት ምክንያትና በታላቁ ተልእኮ መረዳት ከቦታ ቦታ ወንጌልን ለማሰራጨት ተበታትነው ሲዘሩ፥ ጌታ መንፈስ ቅዱስ እንደ መራቸው በሚሄዱበት አካባቢ ብቁ ሰዎች ሲያገኙ ሽማግሌዎችን እያደራጁና እየሾሙ መሠረታዊ መዋቅር በመጣል የአመራርን ጅምር ባህል አስፋፍተዋል ማለት ይቻላል። ሆኖም ለእገሌ ቀለብ ይከፈላል፥ ለእገሌ ደግሞ አይከፈልም፥ እገሌ ሙሉ ጊዜውን የሰጠ ነው፥ ሌላው ደግሞ ጎደሎ ጊዜውን፥ ብለው ፈጽሞ አላሰተማሩም። እነርሱም ቀለብ አልጠየቁም።

ለምሳሌ፡- እነ ሐዋርያው ጳውሎስ ድንኳን እየሰፉ ራሳቸውን ይደጉሙ እንደነበር በግልጽ ማወቅ ይቻላል። የመደበኛ ደመወዝ ነገር ከሆነ ሙሉ ጊዜ የሚያሰኘው የተጠቀሰም ነገር የለም። እንዲያውም ጳውሎስ የአይሁድ ረቢዎች/ መምህራን ከሚያደርጉት

ተግባር ልምምድ ሳይሆን አይቀርም ራሱን ለመቻል ድንኳን ይሰፋ የነበረው ይባላል። ረቢ ሂሌል (Rabbi Hillel)* የተባለውን ዋናውን የአይሁድ ትምህርት ቤት መሥራች «በወደቁ ዛፎች ተግባር» ላይ ተሠማርቶ ይሠራ የነበረ ነበር ይባላል።

የሚያበራየውን በራ አፉን አለማሰር በእጅ አዙር ለወንጌል ቀለብ አከፋፈልን የሚያሳይ አባባል እንጂ ደመወዝ የሚባል ነገር ተተምኖ አልነበረም። እንዲያውም ያላቸውን ሁሉ በአንድ ላይ አድርገው ማናቸውም እንደሚያስፈልገው መጠን ለእያንዳንዱ ያካፍሉትም ነበር። (የሐዋርያት ሥራ 4፥32-36ን ይመልከቱ)። ገንዘባቸው ሁሉ በአንድነት ነበር እንጂ ካለው አንድ ነገር ስንኳ የራሱ እንደሆነ ማንም አልተናገረም ነበር። ይህ እንግዲህ ቤተ ሰባዊ አስተዳደር ነበር እንጂ፥ ለሙሉ ጊዜ አገልጋይ ቀለብ መስፈርን አያመለክትም። ከዚያም በኋላ የነበሩ አገልጋዮችም ለረጅም ጊዜ እንደዚህ ባለ ሁኔታ ራሳቸውን ለመደጎም የንግድ ተግባር ሲያከናውኑ (ብዙዎችም ነጋዴ ስለነበሩ) ሥራው እንዳይበደል ተብሎ ወደ አራተኛው ምእተ ዓመት ገደማ መደበኛ ቀለብ እንዲሰፈር ይደረግ እንደ ነበር ቀደም ሲል ለመግለጽ ተሞክሯል።

ዋናው ነገር ትክክለኛና ጠቃሚ ሰዓት/ጊዜ (Effective hours) ለጌታ መስጠታችን ነው እንጂ ሙሉ ጊዜ፥ ጎዶሎ ጊዜ፥ ወይም የትርፍ ጊዜ አገልጋይ፥ «የጊዜ አተላ» የሰጡ ብሎ አገልጋዩንና አገልግሎትን ማንቂሸሽ ወይም መተቸት ነውር ነው። እንዲያውም አንድ ጊዜ አንድ ጸሐፊ [በሕይወት መጽሔት ቁጥር 39፥ ሕዳር 1991፥ ገጽ፡27] ውስጥ እንዲህ ብለው ነበር፤ *«አገልግሎት በሰጠታ ላይ ይመሥረት፥ እግዚአብሔር ለቦታው የጠራቸው ይምሩን፥ እግዚአብሔር ለእረኝነት አገልግሎት የጠራቸውና ሙሉ ጊዜያቸውን የሰጡ ሰዎች የሚፈጽሙት እንጂ <u>የጊዜ አተላ</u> ለጌታ የሚሰጡ ሰዎች መሆን የለበትም»* ብለዋል። አባባላቸው የሚገርም ነው። አተላ ሁል ጊዜ የሚደፉ እንጂ ጥቅም ላይ የሚውል አይደለም። እንደ አተላ የተቆጠረ ጊዜ አይጠቅምም። እውነተኛ የጌታ ባርያ የሆነ ሁሉ ደግሞ ለአምላኩ አተላ የሆነ ስጦታ አያቀርብም ብዬ በሙሉ ልብ መናገር እችላለሁ።

---

* Neil, Braun, *"Laity Mobilization"*, (William E. Pub. USA, 1971), P. 35.

እንዲህ እንደ ተጻፈ፥ «*በአምላክህ በእግዚአብሔር ፊት የተጠላ ነውና ነውር ወይም ክፉ ነገር ያለበትን---ለአምላክህ ለእግዚአብሔር አትሠዋ።*» (ዘዳግም 17፡1ን ይመልከቱ)። በእርግጥ ይህ ሌላውን የመንቀፍ አባባል የቀራጩንና የፈሪሳዊውን ጸሎት ያስታውሰናል። (ሉቃስ 18፥9–14ን ይመልከቱ)። እግዚአብሔር የጠራቸው «ጠርምስ» የሚባሉትን ዓይነት ዘመን ያመጣው ቀውስ አይፈጽሙም። የእርሱን ጊዜ ይጠብቃሉ። እርሱ ሊያስቀምጣቸው ከፈለገ ማን ከልክሏቸው? በጉልበት ወይም መፈንቅለ ሥርዓት ማድረግ የጽድቅ መንገድ አይደለም። መንፈሳዊ ሥልጣን ከዓለማዊ ሥርዓት የምንማረው አይደለም።

እንዲያውም ይህን ጥቅስ መመልከት መልካም ይመስለኛል። በማቴዎስ ወንጌል 20፡1–16 እንደ ተጠቀሰው ጥዋት ጀመሩ በአሥራ አንደኛው ሰዓት፥ ቀኑን ሁሉ ሠሩ ወይም ጥቂት ሠሩ የወይኑ አትክልት ጌታ ሥራው ላይ የተሰማሩትን ሁሉ እኩል አደላድሎ ይከፍላል። ቁም ነገሩ ሥራው ላይ ሲያላዝኑ መዋሉ ሳይሆን ውጤት ማስመዝገቡ ነው። እነዚያ የትርፍ ጊዜ አገልጋዮች ቢመስሉም ለጌታ ያላቸውን ሩጫ የሚተምነው ራሱ ባለቤቱ መድኃኒዓለም ነው። የሙሉ ጊዜ ሰጪዎችንም የሚመዝነው ያው ራሱ ጌታ ነው።

እነዚያ «ሯጮች» ባይሆኑም ቁጭ ብለው ለጌታ ሥራ መከፈል የሚገባውን በመክፈል፥ ማደራጀትና ማዘጋጀት የሚገባውን በማዘጋጀት፥ አቅማቸው የፈቀደውን በቅንነት ከሠሩ ከዚያም ሲያልፍ በመጸለይ ድርሻቸውን ከተወጡ ምን አነሳቸው? ስለ ምንስ ይነቀፋሉ? እንደ እውነቱ ከሆነ የሰው ልጆች ከሚሠሩበት ሰዓት ይልቅ የሚተጉበት እንደሚያመዝን ጥናቶች ያስረዳሉ። ሐዋርያት እንኳን ጌታ በጸሎት ሲጋደል እነርሱ እንቅልፍ ከብዶቸው ነበር። በእነጳውሎስ ዘመን እንቅልፍ ማጣትም አንድ አገልግሎት ሳይሆን አይቀርም። (2ኛ ቆሮንቶስ 11፥ 27ን ይመልከቱ)። ነገሩ ከትጋቱ ነው እንጂ ከወኔውና ከሥራ መደቡ አይደለም። እንደ ወኔው ቢሆንማ ጴጥሮስ ጌታን ባልካደ ነበር።

መጽሐፉ እንደሚል አንዱ ያጠጣል፤ ሌላው ደግሞ ይኮተኩታል፥ እግዚአብሔርም ያሳድጋል። የሚያሳድግ እግዚአብሔር ነው እንጂ ፓስተር አይደለም። በሕይወት ቁጥር 46 ውስጥ፥ እንደ ገና «*---ወልዶና አሳድጎ ደቀ መዝሙር በማድረግ ለአገልግሎት የሚያበቃ እረኛ ማግኘት ግድ ይሆንብናል*» ብለው ጸሐፊው ያቀረቡት አጠያያቂ ነው። ቃሉ እንደሚል ግን የሚያሳድግ እግዚአብሔር እንጂ እረኛ

አይደለም። (1ኛ ቆሮንቶስ 3፥6-7 ይመልከቱ)። ይህ ነው እንግዲህ እውነተኛው የእግዚአብሔር ቤት አሠራር።

መቼም «ለራስ ሲቆርሱ አያላንሱ» ነውና የሙሉ ጊዜ አገልጋዮችን ነፃ ለማውጣት የሚታገሉ ሰዎች መጽሐፉ ያላለውን ወደ መጽሐፉ ውስጥ እያነበቡ ያልሆነውን ሆነ በማለት ክፉ ዘር ይዘራሉ። ለእግዚአብሔር ግን እንደ ሙሉ ጊዜው ሁሉ ትርፍ ጊዜውንም የሰጠው አስፈላጊ ነው። ያ ባለትርፍ ጊዜው ሠርቶ ገንዘብ ካላመጣ ሁሉም የሙሉ ጊዜ አገልጋዮች ቢሆኑ በምን ሊኖሩ ነው? ችግርስ ያመጣው ይኼው አይደል? ይህ እንግዲህ ሚዛን የጎደለው አመለካከት ሲሆን መጽሐፍ ቅዱሳዊም አይደለም። አገልጋይ ሁሉ ሥራውን እየተወ ሙሉ ጊዜውን በመስጠት እንደ ሌዋዊ ርስት አይኑረው አልተባለም። ሥራውን እየሠራ በሚገባ ማገልገል ይችላል። ለመሆኑ አገልጋይ ለመባል ሙሉ ጊዜ መሰጠት አለበት የተባለው መቼ ነው?

ይህ ነገር የገባቸው አፄ ቴዎድሮስ እንኳን በአሞር ተቀጩ እንጂ በየቤተ ክርስቲያኑ/ሰበካ ጉባኤ የቄሶችን ቁጥር በሁለት ወስነው ሌሎቹ ወደ ተግባር እንዲሰማሩ ሊያደርጉ ጀምረው ነበር ይባላል። ዋናው ነገር ለጌታ መሰጠት ነው እንጂ የሥራ ዘርፉ መደብ ወይም ክፍል አይደለም።

ሙሉ ጊዜ መስጠት «አንጻራዊ» ካልሆነ እነ ጳውሎስ ሙሉ ጊዜ ሰጥተዋል ካልን ድንኳን ይሰፉበት የነበረው ሰዓት ምን ሊባል ይሆን? ሙሉ ጊዜ ማለት ለመሆኑ ስንት ሰዓት ነው? እንዲያውም ጳውሎስ ያልሠራ አይብላ ያለው አንዳንድ ወገኖች ምንም ሥራ ሳይሠሩ ቤት ለቤት እየዞሩ (አንዳንዶች አሁን እንደሚያደርጉት ማለት ነው) ሲያስቸግሩ ተገንዝቦ መሆኑን በ2ኛ ተሰሎንቄ 3፥6-13 ማንበብ ለአብነት ይበቃል።

እንደተባለ፦

> *«---እኛን ልትመስሉ እንዴት እንደሚገባችሁ ራሳችሁ ታውቃላችሁና፥ በእናንተ ዘንድ ያለ ሥርዓት አልሄድንምና፥ ከእናንተ ዘንድ በአንዱ ስንኳ እንዳንከብድበት፥ ሌሊትና ቀን በድካምና በጥረት እየሠራን እንኖር ነበር እንጂ፥ ከማንም እንጀራን እንዲያው አልበላንምና።»* (/ቁጥር 7-8 ይመልከቱ)።

አሠራት የሌዋዊ ቀለብ ነው፥ አሠራታችሁን አምጡ እያሉ በሄዱበት ሁሉ ዝርፊያ አላካሄዱም። ጳውሎስ ይህንን ነገር ሲጽፍ ያለ ሥርዓት የሚሄዱ እንደነበሩ ሰምቶ ነበር። ሙሉ ጊዜ ተሰጠ ማለት 24 ሰዓታትን ተቀምጦ ማጥፋት እኮ አይደለም። ልብን የሚመዝን

ጌታ የሁሉንም ሩጫ ይመለከታል። ግማሹ ለቀለብ፥ ግማሹ ለሥልጣን፥ ሌላው ደግሞ በንጹህ ልቡ ለወንጌል መሮጡን በደንብ ያውቃል፤ ያያልም። አስተዋይ ግን ጊዜውን ሳይሆን ራሱን ይመዝናል።

ወንጌልን የሥራ መስክ አድርጎ ማየትና በወንጌል ስም ቀለብ ማግኘት እውነተኛ ሠራተኛ፥ ሐቀኛ የጌታ ባሪያ አያደርግም። ይህን በተሞክሮ አይተነዋል። አሁንማ የሥራ መስክ እየሆነ ስለመጣ ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች እጅግ ፈታኝ ወቅት የሆነ ይመስለኛል። ወንጌል ደግሞ ከእንጀራ ጋር ከተያያዘ መበረዙ አይቀሬ ነው። የሚያሰጋውም ይኼው ነው። መክፈል የማይችሉ አነስተኛ ቤተ ክርስቲያናት ምን ይበጃቸው ይሆን? እንደዚህ ባለ ሁኔታ እግዚአብሔር «ባሪያዬ ሙሴ (ኢያሱ 1፥2)፥ ባሪያዬ ኢያሱ (ኢያሱ 24፥29)፥ የታመነው ምስክሬ አንቲጳስ (ራእይ 2፥13)፥ ወዘተ...» የሚለውን ዓይነት ሰው ማግኘት አዳጋች ይሆናል። ፈሪሳውያን ራሳቸውን በሚያጸድቁበት ዘመን የጌታ መልአክ ወደ ቤተ መቅደሱ አገልጋዮች ሳይሆን ወደ አናጺው ወደ ዮሴፍ ነበር የተላከው። (ማቴዎስ 1፥20-25ን ይመልከቱ)።

በሌላው ዓለም አንድ የሰማሁትና ያረጋገጥኩት የሥራ ልምምድ አለ። አንዳንድ ሰዎች በተለይም ወጣቶች ምቹ ጊዜ ሲሆንላቸው የአሜሪካን ግዛት ወደ ሆነችው አላስካ ለጉልበት ሥራ ይሄዱና ዓሣ እያጠመዱ ሽጠው ገንዘብ በማጠራቀም በሌላ ወቅት ለወንጌል ተግባር ይሰማራሉ። ራሳቸውን በራሳቸው ያስተዳድራሉ። ይህን የተማሩት ከእነ ጳውሎስ ይመስለኛል። በሌላው ትከሻ ላይ እየኖሩ መቀናጣት አይሹም፤ የወንጌል እንጂ የቀለብ እስረኛ አይሆኑም። ደፍረው ለመገሠጽና ለማስተማርም የሚገድባቸው ነገር አይኖርም።

ጳውሎስ በሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 20፥33-35 ውስጥ እንዲህ ብሏል፤ *«---ከማንም ብር ወይም ወርቅ ወይም ልብስ አልተመኘሁም። እነዚህ እጆቼ በሚያስፈልገኝ ነገር ለእኔና ከእኔ ጋር ላሉት እንዳገለገሉ እናንተ ታውቃላችሁ። እንዲሁ እየደከማችሁ ---የጌታን የኢየሱስን ቃል ልታስቡ ይገባችሁ ዘንድ በሁሉ አሳየኋችሁ።»*

ቀለብ መብት ቢሆንም ቅሉ መብቴ ነው ብሎ በመብቱ ለመጠቀም አልተሟገተም፤ ሌሎችንም አላሳደመም። በምዕራፍ 18፥3 ውስጥ ደግሞ እንደምናነበው፥

«---ሥራቸው አንድ ስለ ነበረ በእነርሱ ዘንድ ተቀምጦ በአንድ ላይ ሠሩ፥ ሥራቸውም ድንኳን መስፋት ነበርና» ይላል።

አንዳንዱ የሙሉ ጊዜ ሠራተኛ ነኝ ብለው ሥራ ለመሥራት የሚጠሉና ሥራውን «አናቴማ» ወይም የተረገመ ነው የሚሉ አገልጋዮች ይህንን ጥቅስ እንዴት ይረዱት ይሆን? ለቃሉ መትጋት ሥራን እንዳይሠሩ እንደማያደርግ ቁጥር 5 ውስጥ መመልከት ይቻላል። ራስን ለመደገም አቅማችን የሚፈቅድ ከሆነ ብንሠራ ምን ክፋት ይኖርበታል? ይህ የሁል ጊዜ ጥያቄዬ ነው። በልበ ሙሉነት የሙሉ ጊዜ ሠራተኛ ነኝ ብሎ በግድ ራስን ማሰር ምንኛ የሚደገፍ ነገር እንደሆነ አልገባኝም። ነገርን ሁሉ መንፈሳዊ አድርገን ከማሰብና «ለሥራ ከመመንኮስ» ሚዛናዊ አመለካከት ቢኖረን የሚበጅ ይመስለኛል። ለነገሩማ ሥራ ክቡር ነው ተብሎ አልነበር? ክቡር የሚሆነው ግን ስንሠራበት እንጂ ቁጭ ብለን ስናሞጋግሰው አይደለም።

በሕያው ቃል ትርጉም እንደዚህ ይላል፥

> *«በጸጥታና በእርጋታ ኑሩ። የራሳችሁን ሥራ እንደሚገባ የምትፈጽሙበትን መንገድ ብቻ አሰቡ። ከዚህ በፊት እንደነገርናችሁ፡ በገዛ እጃችሁ እየሠራችሁ ለኑሮ የሚያስፈልጋችሁን ለማግኘት ተጣጣሩ። ይህንን ብታደርጉ የማንም ሰው ጥገኛ ሳትሆኑ ለመኖር ትችላላችሁ። በጌታ ባላመኑ ሰዎች ዘንድም የተከበራችሁ ትሆናላችሁ»* (1ኛ ተሰሎንቄ 4፡11-12ን ይመልከቱ)።

በመሠረቱ ዋና ተግባራቸውን ወደ ጎን ትተው ሁልጊዜ ይህን ተግባር ያከናውኑ የሚል እምነት የለኝም። አገልግሎቱ ሰፍቶ ሙሉ ጊዜን ከጠየቀ፥ ባለ ሙሉ ጊዜው በታማኝነት ያንን ሙሉ ጊዜ ከሠራበት ምንም ተቃውሞ አይኖረኝም። ነገሮች ሲያስፈሯቸውና የማያዋጣቸው ሆኖ ሲገኝ አቅጣጫ ለመቀየር ለሙሉ ጊዜ አገልግሎት ወጣሁ ማለት ግን አጠያያቂ ነው።

ፓስተር፥ ወንጌላዊ፥ ሽማግሌ፥ ወዘተ... እየተባለ ያለ ትክክለኛ ተግባሩ *(Functions)* የሚቀመጡትንና ቢሮ ጠባቂ የሆኑትን ግን እጠይቃለሁ። ከመንጋው ተለይቶ ያለ እረኛ ምን ዓይነት እረኛ/መጋቢ ነው? ከመንጋው ተለይቶ እንዴትስ እረኛ ነኝ ይላል። መጋቢነቱስ ለሥልጣን ነው ወይስ ለመንጋው እረኝነት? የመንጋውን መግባትና መውጣት በቅርበት የማይከታተል፥ በሩቅ የመቆጣጠሪያ መሣሪያ *(Remote Control)* የሚካሄድ ፓስተርነት/እረኝነት ምን ዓይነት ነው? እረኛ ከመንጋው ከተለየ እረኛ ሊባል ይችላል ወይ? በእርግጥ «እረኛ ነበር» ሊባል ይችላል። በመሆኑም መጋቢነት የአገልግሎት ተግባር ነው እንጂ የማዕረግ ሹመት አይደለም። አንድ

ሰው የመጋቢነቱን ተግባር እስካላከናወነና መንጋውንም ዕለት በዕለት በቅርብ እስካልተከታተለ መጋቢ ነኝ ቢል ራሱን ያታልላል። መጽሐፍ ቅዱሳዊም አይመስለኝም።

በአጠቃላይ ግን አቅማቸው ከፈቀደና ጊዜ ካገኙ ያለ ሥራ ከመቀመጥና በከንቱ ዘመን ከማሳለፍ ተጨማሪ ተግባር ቢያከናውኑ እጅግ የሚጠቀሙ ይመስለኛል። ምክንያቱም ተግባር በመፍታት ጣሪያ ይጎብጣልና። ያልሆነ ባሕርይ ይለመድና «ልጁን ልታፋታ እንዳሰበችው አማት» መሆን ይመጣል። በዚህም ሁኔታ በተግባር ከተጠመዱ ራስን መደጎምና ከቤተ ክርስቲያን በሚሰፈር ቀለብ ላይ ብቻ ተስፋ ከማድረግ ይድናሉ።

የቀለብ ነገር በመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን አጀንዳዋ የሆነበት ዘመን አልነበረም። ዊሊያም ራምሴይ የተባለ ጸሐፊ እንደሚናገረው በአራተኛው ምእተ ዓመት መጨረሻ አካባቢ እንኳን በንግድ ተግባር ይተዳደሩ የነበሩ ካህናት እንደነበሩና የዕለት እንጀራቸውንም ለማግኘት የእጅ ሥራዎችን ጭምር ይሠሩ እንደነበር ጠቅሷል።

ጳውሎስም ድንኳን መስፋት መተዳደሪያው የነበረው ቋሚ ገቢ ስላልነበረውና የአይሁድ መምህራን (ራቢዎች) ይህንኑ ያደርጉ ስለነበር ከእነርሱ ልምምድ ተምሮ ሊሆን እንደሚችል ተጠቅሷል። ለምሳሌ፡- የአይሁዶችን ዋናውን ትምህርት ቤት መሥራች የነበረው (Rabbi Hillel)ን ቀደም ሲል ጠቅሻለሁ። እንደዚህ ያለው ልምምድ የሙሉ ጊዜ ሠራተኛውን ተጨሪና በሌሎች ተመጽዋች አያደርገውም። በዚህም ለእንጀራው ሳይሆን ለጥሪው መቆም ይችላል።

በሌሎች አገርም ያለው ተቀጥሮ የማገልገል ልምድ ከፉ አይደለም። ምክንያቱም ልቀቅ ሲባል አተካሮ ሳያመጣ፥ አንድ መጋቢ እንዳሉት «ምድርንም ሳያናውጥ» በቀላሉ ይለቃል። ምእመን እያተራመሰ ቤተ ክርስቲያንን አይከፋፍልም። በተለይ በሠለጠኑት አገሮች ሌላ ተጨማሪ ሥራ ለመሥራት ስለሚያዳግታቸው ተቀጥሮ የሚሠራ ፓስተር መመደብ የተለመደ ነው።

እንደ ኒል ብራውን አባባል፥

> "In Japanese churches today, the role of the layman is too often limited to bringing to the services his ears to hear the pastor's sermon and his wallet to support the budget".[3]

«ዛሬ በጃፓናውያን ቤተ ክርስቲያን የአንድ ምእመን ኃላፊነት/ተግባር የፓስተሩን መልእክት ለመስማት ጆሮውን፥

በጀቱንም ለመደገፍ የገንዘብ ቦርሳውን ማምጣት ነው» ብሏል። ይህም እንግዲህ የሚሆነው ፓስተሩ ሁሉን ልጠቅልል ሲልና የእያንዳንዱ ምእመን እንደ ቤተ ክርስቲያን አካልነቱ ተግባሩን መፈጸም ሲያቅተው ነው።

በእርግጥ አዲስ አካባቢ ሄዶ ብቁ አገልጋዮች እስኪገኙ ድረስ ያ ወንጌላዊ ወይም ፓስተር ነገሮችን ለጊዜው መቆጣጠሩ አስፈላጊና የሚገባም ይመስለኛል። ሌሎች በሰበሰቧቸው ምእመናን ላይ እጅ ዘርግቶ ያለ ፓስተር የሚሆን ነገር የለም ማለት ቅድመ-አዳም ባሕርይ እንጂ የሁለተኛው አዳም ዘር ባሕርይ አይደለም። የአንድ ሰው ጎልቶ መታየት፥ «ኮከብ» ለመሆን መሻትና ነገሮችን ለመቆጣጠር መሞከር ውጤቱ ቤተ ክርስቲያንን ያዳክማል፤ ገፋ ሲልም ያጠፋል። ዕድገት ሳይታይ ቢሮ ውስጥ ተቀምጦ ይቀራል። የኋላ ኋላ የቤተ ክርስቲያን መቀጨጭም ይከሰታል።

ስለዚህ ይላል ሚ/ር ብራውን፡-

"The churches in the world which experience great growth are frequently those in which personal evangelism is carried-out on a wide scale by un-paid, un-ordained believers."[4]

«በዓለም ላይ መጠነ ሰፊ ዕድገትን የሚለማመዱ ቤተ ክርስቲያናት የወንጌል ስርጭትን ክፍያ በማይሰጣቸውና ባልቀሰሱ አማኞች ደረጃ በስፋት የሚያካሂዱት ናቸው» ይላል። ይህ ሰው በምእመናን ተሳትፎ ላይ ሲናገር፥

"The appointment to Pastoral functions is nowhere in the New Testament limited to persons who receive a salary from the church or who possesses certain educational qualifications".[5]

«ፓስተርነት ከቤተ ክርስቲያን ቀለብ ለሚያገኙ ወይም ለተማሩ ሰዎች ብቻ የተመደበ ሙያ መሆኑን የሚጠቁም ክፍል በየትም ቦታ በአዲስ ኪዳን ውስጥ አይኖርም» ብሏል። ይህ ደግሞ ሐቀኛ ድምዳሜ ይመስላል።

ትልቁ የላቲን አሜሪካን የቤተ ክርስቲያን ዕድገት ምሥጢርም ይኼው የአባላት ተሳትፎ ነው ይባላል። በእኛም አገር በተለይ ከ1960-1970 ዓ. ም. የነበረው ልምምድ ከዚህ የተለየ አልነበረም። ታሪክ ሳይሆን ጸሐፊውም በዚያ ውስጥ ስላለፈ እማኝ ሊሆን ይችላል።

በዚህም ሁኔታ ደቦኛ (ወቅታዊ ረዳቶች) ሳይሆን እውነተኛ ደቀ መዛሙርት ማፍራት ይቻላል።

ቀደም ሲልም እንደተጠቀሰው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ መሪዎች የተሰጡት «---ቅዱሳን አገልግሎትን ለመሥራትና ለክርስቶስም አካል ሕንፃ ፍጹማን ይሆኑ ዘንድ» ምእመኑን ወደ ከፍተኛ ደረጃ ለማድረስ/ብቃት ለማስገኘት ነው። (ኤፌሶን 4፥11ን ይመልከቱ)። መሪዎች ምእመኑን ለአገልግሎት ሥራ ማብቃትና ማዘጋጀት እንዲሁም ማሰማራት ይጠበቅባቸዋል። በዚህም ጥቅስ መሠረት መሪዎች በተለይም (ሽማግሌዎችና ፓስተሮች) ሥራቸው ተመሳሳይ ሆኖ ቅዱሳን ለአገልግሎት እንዲዘጋጁ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። በመሆኑም የክርስቶስ አካል ተግባቡቶ ተግባሩን በሥርዓት እንዲወጣ/እንዲያካሂድ ይደረጋል።

በመሪነት በቤተ ክርስቲያን የሚሾሙ ሽማግሌዎች ሁል ጊዜ በብዙ ቁጥር ናቸው። (የሐዋርያት ሥራ 14፥23፤ 15፡4፥6፥22፥23፥ እና 20፡17፥18፥ ፊልጵስዮስ 1፥1፤ ቲቶ 1፥5 እና ያዕቆብ 5፥14ን ይመልከቱ)። ለዚህም ነው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከማንኛውም የአመራር ዘይቤ ይልቅ የጋራ (የጥምር) አመራር ተደጋፊነት የሚኖረው። የአንድ ሰው ዝናና የበላይነትም ገንኖ አይወጣም። ለምሳሌ፡- በእግር ኳስ ጨዋታ ቡድን በጥቅል አሸነፈ ይባላል እንጂ (ሰባት ቁጥሩ፥ ስምንት ቁጥሩ፥ ወዘተ...) ድል አደረገ አይባልም። የአንዱ ድል የሌላውም ድል ነውና። የወል አሠራርና ድርሻ ያ ነው። ሽልማቱም በጋራ ነው።

አሁን አሁንማ ይህ «ፓስተር፥ ፓስተር፤ ሽማግሌ፥ ሽማግሌ» የሚሉት ነገር አገልግሎት ሳይሆን የሥልጣን ሹመት እየሆነ የመጣ ይመስላል። ሰውም ስሙን ሲተዋወቅ እንዳይቀርበት «ፓስተር እገሌ» ነኝ ይላል። «አቶ እገሌ፥ ጓድ እገሌ» ነኝ እንደሚሉት ማለት ነው። ሰውም ሲጠራቸው ፓስተር ካልተባሉ ቅሬታ ይከተላል። እኔስ ይህ አዝማሚያ እያስፈራኝ ነው። በእርግጥ የሰውን ክብር መዘርጠጥን መደገፌ ሳይሆን፥ ከልክ ያለፈ የስም ላይ ተቀጥላ እያሳሰበኝ ስለመጣ ነው። ክብር ለሚገባውማ ክብር መስጠት ተገቢ እንደሆነ መጽሐፉም ያስተምራል። የራስን ክብር መፈለግ ግን እንደማያስከብር ደግሞ ይናገራል። (ምሳሌ 25፥27ን ይመልከቱ)። በአጠቃላይ የሰው ልጅ ዝናንና ክብርን ከመቋቋም ይልቅ መከራና ችግርን መቋቋም የሚቀልለው ይመስለኛል። መፈተን ያለ ነውና መጠንቀቅ ግን ይጠቅማል።

ጌታ መምህር መምህር ተብላችሁ አትጠሩ፤ መምህራችሁ አንዱ ነውና፥ ሊቃችሁ አንዱ ክርስቶስ ነውና ሊቃውንት ተብላችሁ አትጠሩ ብሎ በማቴዎስ 23፡7-8 የጠቀሰውን ለሌሎች መቃወሚያ እንጠቀምበታለን። ምን ነው እኛስ የራሳችንን አላየንም? በመሠረቱ ተግባሩ ለፓስተርነት ካበቃው አንድ ሰው ፓስተር ባይባል ምን ይሆናል? ቤተ ክርስቲያኗ አትዘጋም እኮ! በእኛ አገር አልተለመድም እንጂ እንደ ሥልጣን መጠቀም እንደ ኮሪያ ባሉት አገሮች እንዳይቀርባቸው ሽማግሌዎችም፥ «ሽማግሌ እከሌ!» *(Elder so and so!)* እየተባሉ ነው የሚጠሩት። ይህ ጉዳይ አጠያያቂ ይመስለኛል። ጌታ ሰዎችን ለቤተ ክርስቲያን ስጦታ የሰጠው ሥራውን እንዲሠሩ እንጂ ለግል መከበሪያ፥ ድርጅት ለመክፈቻ ወይም ለሥልጣን አይደለም። ስለሆነም ለመልካም አገልግሎት ለቤተ ክርስቲያን የተሰጠው ስጦታ የግል መበልጸጊያችንና መታወቂያችን መሆን አይገባውም። ስለዚህ ይህ ነገር ጥንቃቄ ይጠይቃል።

በተጨማሪ ዊልያም ናብ እንዲሉት፡-

"...true biblical leadership is not 'one pastor' system but rather consists of plural leadership. This shared leadership structure best promotes and protects the vitality of the New Covenant Priesthood." [Internet: 1999,P.1].

ትርጉሙም፥ «---እውነተኛው መጽሐፍ ቅዱሳዊ አመራር 'የአንድ መጋቢ/ፓስተር' አሠራር ዘዴ ሳይሆን የወል አመራር ነው። ይህም የተከፋፈለ/የጋራ አመራር ሥርዓት አዲሱን የክህነት ቃል ኪዳን አስፈላጊነትን ያራምዳል፤ ጠብቆም ያቆየዋል» ብለዋል።

መጽሐፍ ቅዱሳዊው አመራር የአንድ ሰው ማለትም የፓስተር ወይም የሽማግሌ አመራር ዘዴን አይጠቁምም። ነገር ግን ሁሉም በጋራ/በወል የሚያስተዳድሩበት ነው። ይህ ለብዙኀን የተከፋፈለ የአመራር መዋቅር የአዲሱን የክህነት ቃል ኪዳን አስፈላጊነት ያስፋፋል፤ ይጠብቃል። መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚነግረን በጌታ በኢየሱስ ያመኑ/ምእመናን ሁሉ፥ ካህናት ያውም የንጉሥ ካህናት ናቸው። ሐዋርያው ጴጥሮስ እንዳለው፡-

«እናንተ ግን ከጨለማ ወደሚደነቅ ብርሃኑ የጠራችሁን የእርሱን በጎነት እንድትነግሩ የተመረጠ ትውልድ፥ <u>የንጉሥ ካህናት</u>፥ ቅዱስ ሕዝብ፥ ለርስቱ የተለየ ወገን ናችሁ፤ እናንተ ቀድሞ ወገን አልነበራችሁም፤ አሁን ግን የእግዚአብሔር ወገን ናችሁ፤ እናንተ

ምሕረት ያገኛችሁ አልነበራችሁም፥ አሁን ግን ምሕረትን አግኝታችኋል።» (1ኛ ጴጥሮስ 2፥9-10ን ይመልከቱ)።

ስለዚህ ማወቅ ያለብን ሁሉም የእግዚአብሔር ሕዝብ ካህን እንዲያውም የንጉሥ ካህን ሲሆን ሊቀ ካህኑም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እንጂ ማንም አይደለም። በብሉይ ኪዳን *«---ከህሃኑን ለሰጠታ አገልግሎት ሰጥቼአችኋለሁ»* እንደ ተባለ ለእኛም ለአዲስ ኪዳን ካህናት ተሰጥቶናል። (ዘኁልቁ 18፥7ን ይመልከቱ)። ሁላችን ካህናት ነን፤ አንዱ ከአንዱ የሚሻልበት የለም። ጸጋው ለሁሉም እኩል ነውና። መካከለኛውም እርሱ ብቻ ነው። ሌላ አያስፈልገንም።

እግዚአብሔር ለአንዱ ቀርቦ ለሌላው የሚርቅ አይደለም። ለመሪዎች የሚሠራ ጌታ ለምእመናንም ይሠራል። ለፓስተር የሚሠራ ጌታ ለሽማግሌውም ያው ነው። እንዲህ ተብሎ እንደ ተጻፈ፥ *«---እግዚአብሔር ሁሉን ይምር ዘንድ ሁሉን በአለመታዘዝ ዘግቶታልና።»* (ሮሜ 11፥32ን ይመልከቱ)። እግዚአብሔር አንዱን ልጅ አድርጎ ሌላውን የእንጀራ ልጅ አያደርግም። በመሆኑም ወደ ጸጋው ዙፋን የመቅረብ ዕድል በሙላት ለሁሉም ያለማዳላት ተሰጥቷል። እንደ ብሉይ ኪዳን ካህን መካከለኛ ሆኖ ነገራችንን ወደ እግዚአብሔር የሚያቀርብልን «የነፍስ አባት» አያስፈልገንም። ነፍሳችንን የሰጠን ማን ሆኖ ነው የነፍስ አባት የሚያስፈልገን? ይህ ጉዳይ የአዲስ ኪዳንን የክህነት ቃል ኪዳን *(The New Covenant Priesthood)* የሚጻረር ድርጊት ነው። ስለዚህ ወደ እግዚአብሔር መቅረብ የሁሉም አማኝ መብትና ስጦታ ነው።

በቅርቡ እንዲያውም አንድ መራሔ ፓስተር አፍቃሪ የሆኑ ሰው የአሠራር ለውጥ እንዲደረግ በሕይወት መጽሔት ላይ ጥሪ ሲያቀርቡ እንዲህ ብለዋል፦

«---መጋቢያዊ አመራርና አገልግሎት በብሉይ የታየ ቢሆንም በአዲስ ኪዳን ግን በጎላ መልኩ የተገለጠና በተግባር ላይ የዋለ ነው» ---መጋቢያዊ አመራር *(Pastoral Leadership)* ከመለኮታዊ ጥሪና ከስጦታ ጋር የተያያዘ በመሆኑ በተግባርም ተረካቢ ትውልድ ለማፍራት <u>ፍቱንነቱ የተረጋገጠና በመጽሐፍ ቅዱስም የተገለጠ እውነት</u> ስለሆነ ልንከተለው የሚገባን የአሰተዳደር ዓይነት መሆኑን ይህ ጽሑፍ ያሰምርበታል» ብለዋል። (ሕይወት መጽሔት፥ 1992፥ ቁጥር 45 ገጽ 18 እና ቁጥር 46 ገጽ 15ን ይመልከቱ)። ለመሆኑ በየትኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ውስጥ ወይስ በየትኛው አገር ይሆን ፍቱንነቱ የተረጋገጠው?

ባሰመሩበት የአጽንኦት ትምህርታቸውም፥ «በቅድሚያ መታወቅ ያለበት ግን የመጋቢነት አገልግሎት ያለ መጋቢያዊ አመራር ሊከናወን አለመቻሉን ነው» ብለዋል። (ሕይወት ቁ. 46፥ ገጽ 147 ይመልከቱ)። እንደ ጸሐፊው ዕይታ ከሆነ የሽምግልና አስተዳደር ኑፋቄያዊ መስሎ ሳይታያቸው አልቀረም።

ይህንንም የሚጠቁመው ገለጻቸው እንዲህ ይላል፣ «ስለሆነም በዚህ ዘመን ካሉትና በትርፍ ጊዜያቸው ከሚያገለግሉ ሽማግሌዎች ጋር በመጽሐፍ ቅዱስ የተጠቀሱትን ሽማግሌዎች ማዛመድ ለቃሉ ታማኝ አለመሆን ነው። አሁን በሀገራችን ሰዎች የሚሟገቱለትን ሽምግልና መጽሐፍ ቅዱስ አያውቀውም።» (ሕይወት ቁ. 46፥ ገጽ 14 ይመልከቱ)። እርሳቸው እንዳረጋገጡት አባባሉ ይከብዳል። እንደ አባባላቸው የቃሉን እውነት ሳያዛቡ «በትሕትና» ማለት የቻሉትም ይህንኑ ነበር።

ታዲያ በእንዲህ ያለ ሁኔታ ያለውን ፓስተርነቱንስ እግዚአብሔር ያውቀው ይሆን? ፈጽሞ አያውቀውም። መጽሐፍ ቅዱስስ ያረጋገጠውስ ይሆን? በፍጹም። እንደ ተባለ «እኛን በሚቆጣጠር በእርሱ ዓይኖቹ ፊት ሁሉ ነገር የተራቆተና የተገለጠ ነው እንጂ፥ በእርሱ ፊት የተሰወረ ፍጥረት የለም።» (ዕብራውያን 4፥13ን ይመልከቱ)። ኦንደ እኚህ ፓስተርና ጸሐፊ ከሆነ ይህንን የጻፉት የቃሉን እውነት እንዳያዛቡ አስበው ነበር። በእርግጥ ጸሐፊው ራሳቸው ፓስተር ስለሆኑ እጅግም አያስደንቅም። በልባቸው የሞላውን መጻፋቸው ተገቢ ነው። ይህ አያስወቅስም ይሆናል። ተግባራዊውን እውነታ ሳይሆን አንድምታዊ ትንታኔያቸውን ነው ያጸደቁት።

ሆኖም ግን የእኔ መጽሐፍ ቅዱስ ነገሩን እንደዚህ ግልጽ አድርጎ አስቀምጦ አላየሁትም። እንዲያ ቢሆንማ ምን ያከራክራል? እንደዚህ ዓይነት ጽንፈኛ አሳቦች ልምምድን በማስተናገድ የሚከሰቱ እንጂ ከመጽሐፍ ቅዱስ የሚመነጩ አይደሉም። እንደ ጸሐፊው አባባል «አለመጋቢነት አገልግሎት አገልግሎት ሁሉ ላሳር ነው» የሚሉ ይመስላል። ጸሐፊው የሽማግሌዎች ጠበቃ የመጋቢ ባላንጣ አለመሆኑን ግን በግልጽ ለማስቀመጥ ይሻል። ሁለቱም ያው ናቸው። የመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ግን ፈጽሞ መዛባት የለበትም። አገልጋይ ባርያ (Servant Leader) የሆነ በዚህ እሰጥ አገባ ብሎ አታካሮ አይፈጥርም። እቅጩ ይኼው ነውና።

በመሠረቱ ከሽማግሌዎችም ይሁን ከፓስተሮች መስመር የሳተ፥ ፈር የለቀቀ ሙግትና አታካሮ ካለ መጽሐፉ ሁሉንም በአንድ ይፈርጃቸዋል። እንዲያውም ሁሉም ቦታቸውን ለቅቀው መሠረታዊ ትምህርት ቢማሩ ይበጃል። የሚማሩትም ሥነ መለኮት ትምህርት ቤት ገብተው ሳይሆን ከጌታ እግር ሥር ቁጭ በማለትና በማረፍ ቢሆን ይመረጣል። ምክንያቱም ሥነ መለኮት ት/ቤት ባሕርይን ላይለውጥ ይችላልና ነው።

በተጨማሪ ጸሐፊው የሚሟገቱለትን መጋቢያዊ አመራር ሲያወድሱ፥

«መጋቢያዊ አመራር ከተወሰኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በተወሰደ ቁንጽል አሳብ ላይ የተመሠረተ ሳይሆን የብሉይና የአዲስ ኪዳን ድጋፍ ያለው አመለካከት ነው» ብለዋል። (ሕይወት ቁ. 46፥ ገጽ 13ን ይመልከቱ)። ይህ ግን ትክክለኛ ትንታኔ ያለው የመጽሐፍ ቅዱስ እውነት አይደለም። በየትኛውም ትርጉም ቢሆን ግልጽ ድጋፉን እንደዚህ አድርጎ አያስቀምጥም። ይህ ግልጽ የሆነ ስሜትን ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ማንበብ ነው።

ይህን መሰል አተረጓጎምን በሚመለከት ታዋቂው የሪጀንት ኮሌጅ ፕሮፌሰር ጎርደን ፊ እንዲህ ይላሉ፤

> *"Reading the Bible with an eye only to its meaning for us can lead to a great deal of nonsense as well as to every imaginable kind of error-because it lacks control".**

ትርጉሙም፥ «ለእኛ ትርጉም እንዲሰጠን መጽሐፍ ቅዱስን በዓይናችን ብቻ ማንበብ ቁጥጥር ስለሚያንሰው ወደ ትልቅና የማይረባ ግምታዊ የስሕተት ዓይነት ይመራናል።»

ቀደም ሲል እንዳነሣነው ትንታኔ የሚገርመው ደግሞ ይህ የመጋቢነት ባሕርይ የሚመነጨው ከእግዚአብሔር ባሕርይ ነው ብለዋል። የእግዚአብሔር ባሕርይ የሚኖራቸው መጋቢያን ብቻ ናቸው? እውነት ቢሆንማ ምን ችግር ነበር። ይህንንማ እውነተኛና ቅዱስ ባሕርይ ቢያገኝ ኖሮ ማን ደፍሮ ይቃወማል? ጉዳዩ የባሕርይ ነገር ሳይሆን የቤተ ክርስቲያን ሥልጣን አደረጃጀትና አወቃቀር

---

* Gordon D. Fee & Douglas Stuart, *"How To Read The Bible For All Its worth"*, (Zondervan Pub.USA 1982), P.13.

እውነታ ነው። የእግዚአብሔር ባሕርይማ ለሁላችንም እጅግ ያስፈልጋል። የጠፋውስ እርሱ አይደለም? የእግዚአብሔር ባሕርይማ ያለው እርሱ እውነተኛና ቅዱስ የእግዚአብሔር ባሪያ ወይም አገልጋይ ነው። ይህም እንግዲህ ምእመን፥ ፓስተር፥ ወይም ሽማግሌ አይልም። እንደ ትርጉሙማ ቃላትን ለመለጠጥ ካልተፈለገ በስተቀር ልዩነት እንደሌላቸው ቀደም ሲል ባቀረብኩት የቃላት ጥናት ለማስረዳት ተሞክሯል። እንደ ቃሉ ከሆነ አሁንም ፓስተር ሽማግሌ ነው፤ ሽማግሌም ፓስተር ሊሆን ይችላል፤ ነውም።

የመደብ ልዩነቱን እኛ ካልፈጠርነው መደቡስ አልነበረም። የዘርፍ ልዩነት ይኖራል እንጂ የበላይና የበታች የሚያሰኝ ነገር የለም። ሽማግሌ ለመሆን በዲቁና፥ ፓስተር ለመሆን በወንጌላዊና በሽማግሌ ውስጥ ማለፍ አለበት ያለው ማን ነው? የቱስ መጽሐፍ ነው እንደዚያ ብሎ ያስተማረን? ወንጌላዊም እንደ ፓስተር ወይም ሽማግሌ የራሱ ጸጋ የተሰጠው የከበረ አገልግሎት ነው። እንዲያውም የሚደነቅ አገልግሎት ነው! ታዲያ ፓስተርን ከወንጌላዊ ያስበለጠው ማን ነው?

ስለዚህ እንደዚህ ያሉ የሚያደናግሩ ትንታኔዎች መሠረት ሳይኖራቸው ለመድረክ ሊቀርቡ የሚገቡ አልነበሩም። ፓስተርና ሽማግሌ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታ ናቸው እንጂ የሚለያዩበት ገጽታ እምብዛም ጎልቶ የሚወጣ አይደለም። እንደሚመስለኝ የዚህን ዓይነት አመለካከት በመያዛችን ነው ችግር እየገጠመን ያለው። አንድ ሰው ጸጋው ማስተማር ብቻ ከሆነ ስለ ምን ፓስተር ይባላል? እንደ ተሰጠው ጸጋ አስተማሪ ቢባል ምን ይጎድለዋል? ይህ ጉዳይ ከፍተኛ ትኩረት የሚያሻው ይመስለኛል።

በአጠቃላይ ከላይ በተገለጹት የጸሐፊው ትንታኔዎች ለመጋቢያዊ አገልግሎት እጅግ የተቆረቆሩና ለሙግት የቀረቡ አስመስሏቸዋል። በዚህ ነገር መሟገት ሞኝነት ይመስለኛል። የጽደቅንም መንገድ ማቅናት ሳይሆን አባጣ ጎርባጣ ማድረግ ይመስለኛል። እውነት ግን በስሜትና በፍላጎት ወይም በምኞት ተድበስብሳ በማይሆን መድረክ ላይ አትሸፈንም፤ አትሸነፍምም። ምናልባት ብትድበሰበስም ጊዜ አጥርቶ ያወጣታል። በንጹሐን አእምሮ ግን የማይገባ ስንክሳር ቃላትን መሰካካት በደል ነው። ቤተ ክርስቲያንን ይከፋፍላል። ማንኛውም የመከፋፈል አዝማሚያ ደግሞ ሁልጊዜ ከጌታ አይደለም። ይህን እርሳቸውም እንደማይጠፉቸው እገምታለሁ።

እንደ እውነቱ ከሆነ ደካማ አገልጋይ በሽማግሌዎች ውስጥ ካለ፥ በፓስተሮችም ውስጥ ሊኖር እንደሚችል አልጠራጠርም። ከዚህ ሁሉ

ግን እርስ በርስ ተደጋግፎ አንዱ በበረታበት የደከመውን ደግፎ መጓዝ ምንኛ መታደል ነው? የእግዚአብሔር ቤት አካል ሁሉ በጋራ ተግባሩን የሚያከናውንበትና የሚደጋገፍበት እንጂ የጥቂቶች መፈንጫ አይደለም። የአካል ብልት ሁሉ ተሳትፎ ወሳኝ ነው። ይህንን ነው እንግዲህ መጽሐፉ የሚያስተምረው። ምሉዕ የሚሆነውም ያኔ ነው። (1ኛ ቆሮንቶስ 12፥12-26፤ ሮሜ 12፥3-8ን ይመልከቱ)። እንግዲህ *«ማንም የክርስቶስ መሆኑን ተረድቶ ቢሆን፥ ይህን እንደገና በራሱ ይቁጠረው፤ እርሱ የክርስቶስ እንደሆነ እኛ ደግሞ እንዲሁ ነን።»* (2ኛ ቆሮንቶስ 10፥7ን ይመልከቱ)።

ስለዚህ ከአገራችን የቤተ ክርስቲያን ታሪክም እንደ ተረዳነው ቀደም ሲል የወንጌሉ ሥራ እንደሚገባ በስፋት የተጓዘው በ«ባለ ጎደሎ ሰዓት ወይም የትርፍ ጊዜ አገልጋዮች» እንደ ነበር የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው። በመሆኑም የአካሉ ብልት በአንድ ላይ መሥራት የአንድን አካል ብቻ ጥቅም አጉልቶ ከማየት ያድናል። አካል አንድ ነውና፥ ሊነጣጠል አይገባውም፤ ቢነጣጠል በራሱ ሊቆም አይችልም። እጅ ከእግር ተገንጥሎ ብቻዬን እኖራለሁ ቢል ደርቆ ከመሞት ውጪ ፋይዳ የለውም።

መጽሐፍ ቅዱሳዊው አመራር ውስጥ ዋናው መበረታታትና መጎልበት የሚኖርበት የአመራር ዘዴ በሙሉ ጊዜ አገልጋዮች *(Clergy)* እና በትርፍ ጊዜ አገልጋዮች *(Laity)* መካከል ያለውንና የሚኖረውን ልዩነት በማጥበብና ወደ አንድ የአካል ዓይነት ብልት አሠራር እንዲመጡ በማድረግ ጎብረትን በመፍጠር ወይም በማስፋፋት ነው እንጂ በማራራቅ አይደለም። ቁልፍ ከሆኑ የዶክትሪናል ችግሮች በስተቀር ልዩነትን በጎብረት መጠበቅ *(Unity in diversity)* ለማንኛውም አሠራር ጠቃሚ ነው። በዚህ መጽሐፍ ጸሐፊ ግንዛቤ ያ ነው የእግዚአብሔርን መንግሥት ለማስፋፋትና እውነተኛ መልእክተኛ ወይም ኤምባሲ በምድር መፍጠር የሚቻልበት መንገድ።

በዚህም የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ፍላጎትና ዕቅድ ይሳካል የሚል እምነት አለኝ። እንደ ተጻፈ፥ *«---ለወደደን ከኃጢአታችንም በደሙ ላጠበን፥ መንግሥትም ለአምላኩና ለአባቱም ካህናት እንድንሆን ላደረገ፥ ለእርሱ ክብርና ኃይል ይሁን፤ አሜን»* (ራእይ 1:6ን ይመልከቱ)።

ጥንትም በዘጸአት 19፥5-6 ውስጥ እንደተባለው፥

«---አሁንም ቃሌን በእውነት ብትሰሙ ኪዳኔንም ብትጠብቁ፥ ምድር ሁሉ የእኔ ናትና ከአሕዛብ ሁሉ የተመረጠ ርስት ትሆኑኛላችሁ፤ እናንተም የካህናት መንግሥት የተቀደሰም ሕዝብ ትሆኑኛላችሁ» ነበር ፍላጎቱ።

የእስራኤል ልጆች ለእግዚአብሔር የካህናት መንግሥት ነበሩ። እኛም የአዲስ ኪዳን የካህናት መንግሥት ለመሆናችን ጥርጥር የለኝም። ስለዚህ ነው ቤተ ክርስቲያን የሰማያዊ መንግሥት ኤምባሲ ጽ/ቤት ናት ያልኩት። በእርግጥ ይህን አባባል ለመቀበል ፈቃደኛ መሆንን ይጠይቃል። ፈቃድ ብቻም ሳይሆን ዝግጅት ያስፈልጋል።

በዚህ መንገድ አንዱ አካል የሌላውን ድርሻና ስጦታ እያከበረ አካሉን በሚገባ ለመንከባከብና ለማሳደግ ብሎም በሕይወት ለማኖር ይተጋል፤ ይሠራል። ካልሆነ ግን የአካልነት ድርሻውን የማይጫወት አካል ሕመምተኛ (Defective) ይሆናል። ስለዚህ ነው ሳይንቲስቶች እንደሚገምቱት ወደ ፊት የሰው ልጆች በእጅና በእግራቸው ተንቀሳቅሰው ከመሥራት ሲታቀቡና በአእምሮአቸው ብቻ ሲሠሩ እጅ እግራቸው እያነሰ ይሄድና ጭንቅላታቸው (Head & Brain) ትልቅ ይሆናል ብለው የሚገምቱት። ይህ እውነት ሆነም አልሆነም የአካል ብልቶችን የቡድን ሥራ አስፈላጊነት ያስገነዝባል። አካልም ሁሉ በጋራ ሲሠሩ ነገር ሁሉ በትክክል ይሄዳል። ምእመኑ፥ ፓስተርና ሽማግሌዎች ሁሉ በጋራ ቢሠሩ ወንጌል ምንኛ በሮጠ ነበር።

ስለሆነም ማንኛውንም አገልጋይ ለመምረጥ/ለመሾም ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግና በስፋት መጸለይ ተገቢ ይሆናል። አለበለዚያ የማይገባቸው ሰዎች ወደ ሥልጣን ሲመጡ ቤተ ክርስቲያንን ከማተራመስና ምድራዊ ከማድረግ አይታቀቡም። አሁንም ሞልተዋል፤ ገና ወደ ፊትም ይበዛሉ። አንድ ሰው አንድ ጊዜ እንደዚህ ብለዋል፥ «ሥራ አጥቶ ቤተ ክርስቲያን ግቢ ውስጥ ስለዋለ፥ ጡረታ ወጥቶ መሄጃ ሲያጣ ወደ ቤተ ክርስቲያን ግቢ ስለተመላላሰ፥ የአገሌ ልጅ፥ የአገሌ ዘመድ ስለሆነ፥ በቅርቡ ሥነ መለኮታዊ ትምህርት ተምሮ ስለተመረቀ፥ ወዘተ... እያልን በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ ከመሾማችን በፊት ጥንቃቄ ማድረግ ይጠበቅብናል።»

ለወንጌል ሰባኪነት ተጠርተህ ከሆነ ፓስተር መሆንን አትሻ፤ ከእርሱ የምታንስበት ምንም ምክንያት አይኖርም። ፓስተር ለመሆን መንገዱ ወንጌላዊ ወይም ሽማግሌ መሆን አይደለም። ፓስተር የሚያሰኘው ጸጋው እንጂ ሰዎች የሰጡት ሥልጣን አይደለም። ይህ ሊታረም የሚገባ አካሄድ ነው። ሽምግልና ጥሪህ ከሆነም በዚያው ጸጋ

አገልግል። ያለቦታ ገብቶ ሁሉን እችላለሁ ማለት እጅግ ያስገምታል። ማስተዳደርም ቢሆን ለተሰጣቸው እንጂ በጉልበት የሚሆን ነገር አይደለም። ዳሩ ግን የተሟላ ተግባር የሚከናወነው ሁሉም ሲኖሩና በመተጋገዝ ሲሠሩ ብቻ ነው።

«የሙሉ ጊዜ አገልጋይ» የምንለውም ሰው አሽከር ሳይሆን ራሱን ለጌታው መጠቀሚያ አድርጎ በፈቃዱ ያቀረበና መገልገያ መሣሪያ የሆነ እንደ ማለት ነው። ስለሆነም ራሳቸውን በትክክል ለአገልግሎት ያቀረቡ ሰዎች በቂ ደመወዝ የሚከፈላቸው፥ ተገቢው ፍቅርና እንክብካቤ ሊነፈጋቸው የማይገባ ሰዎች ናቸው። የባህል ተጽዕኖ አስገድዶን ይማቅቁ ማለት ግን በደል ነው። እነዚህን ሰዎች እንደ ወንድሞች ማየትና መደገፍ ሲገባ እነርሱም አጸፋውን በትሕትናና በፍቅር ሊመልሱ ይገባል። (1ኛ ቆሮንቶስ 4፥1-2ን ይመልከቱ)። ቃሉ እንደሚል፥ *«ስለዚህ ክርስቶስ ለእግዚአብሔር ክብር እንደ ተቀበላችሁ እንዲሁ እርስ በርሳችሁ ተቀባበሉ።»* (ሮሜ 15፥7 ይመልከቱ)።

ሽማግሌዎች ቀድሞ አጥፍተዋልና አሁን ወቅቱ ደግሞ የፓስተሮች መሆን አለበት ብሎ ያልሆነ የሆነ የሙከራ ጊዜን መፍጠር ተገቢ አይደለም። ሰዎች ናቸውና ሁሉም ያጠፋሉ፤ ሁሉም ይስታሉ። ዳሩ ግን ከእነርሱ የተሻሉ ሰዎች ወደ ቀና መንገድ እየመለሷቸው ቤተ ክርስቲያን ትቀጥላለች። ባይመለሱም እንኳ አትቆምም መሪዋ የሆነ ጌታ ደግሞም የካህን አለቃ አላትና፥ የእረኞች አለቃ በመሆኑ መንጋውን መጠበቅ ያውቅበታል። በአጠቃላይ ሲታይ ግን እንደ ሽማግሌው ፓስተሩም እጅግ አስፈላጊ ነው። የእግዚአብሔር ቤት በቡድን፥ በመተጋገዝና በመያያዝ እንጂ በመነካከስና በመቆሳሰል ብሎም በእኔ እበልጥ በእኔ እበልጥ ፉክክር አትሠራም። ይህ ትልቅ ጉዳት ያስከትላል። ጌታም ያስተማረው ያንኑ ነው ማለት ይቻላል።

ስለዚህ አሁን ያሉት የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በሥርዓትና በአገባቡ አልሠሩምና ብሎ የመጽሐፍ ቅዱስን እውነት ማጣመም ተገቢ አይደለም። ይህ ለዘመናት የቆየን ችግር መፍትሔ አያመጣም። የሁሉም አገልግሎት ያስፈልጋል። ለጋራ ውጤት፥ በንጹሕ ልብና በፍቅር ለመሥራት መነሣሣት እንጂ እኔ እበልጥ እኔ እበልጥ ብሎ ስብከትና መጣጥፍ ቢያበዙ የትም አያደርስም። ድሪቶ ብቻ ይሆናል። እንዲያውም ያስገምታል። ፍቅርና መተሳሰብ ግን ከዚህ ያልፋል። ሕዝቡ አስተዋይ ነውና ለይቶ ያውቃል፤ ምን እንደሚደረግ የማያውቅ ቢመስለንም አሳምሮ ያውቃል። እግዚአብሔርን ስለሚፈራ ብቻ ከመናገር ይታቀባል። በጥናቴ ወቅት የተሰበሰቡትም መጠይቆች

ይህንን በደንብ ያረጋግጣሉ። እያንዳንዱ ሰው ያቀረበው አስተያየት አስገራሚ ሲሆን በጣም ተቀራራቢነትም አለው።

በዓለም ላይ የሚታየው የሥነ ምግባር ብልሽት የሰውን ልጆች የዕለት ተዕለት ሕይወት እያቃወሰ፥ በይቅርታ ፋንታ ጥላቻና ጠብ፥ በደስታ ፋንታ ኀዘንና ልቅሶ፥ በጤንነት ምትክ በሽታና ጉስቁልና፥ ወዘተ. እያቀረበልን ምድራዊ ጉዟችን እንዲበላሽ ይጥራል። አስተዋይ ግን ነገሮችን ይመረምራል። እንደታየውና እንደ አየር ሁኔታ አይነፍስም።

መቼም በእግዚአብሔር ቤት መደጋገፍ እንጂ መገፋፋት የጋራ ጥፋት መሆኑን ካወቅን፥ መመካከርና መስማማት ይሻለናል። *«ነገር ግን እርስ በርሳችሁ ብትነካከሱና ብትበላሉ እርስ በርሳችሁ እንዳትጠፋፉ ተጠንቀቁ»* (ገላትያ 5፡15 ይመልከቱ)። ይህንን ችላ እያልን በራሳችን ዙሪያ ብቻ ብንመላለስ ጉዳት ነው። ውጤቱ በላያችን ጥፋትን ማምጣት ነው። እንደ ተጻፈ፥ *«እነሆ የእኅትሽ የሰዶም ኃጢአት ይህ ነበረ፤ ትዕቢት፥ እንጀራን መጥገብ፥ ፥ መዝለልና ሥራ መፍታት በእርስዋና በሴቶች ልጆችዋ ነበረ፥ የችግረኛውንና የድሀውንም እጅ አላጸናችም። ኮርተው ነበር በፊቴም ርኩስ ነገር አደረጉ፤ ስለዚህ ባየሁ ጊዜ አጠፋኋቸው»* (ሕዝቅኤል 16፡49ን ይመልከቱ)።

የማገናዘቢያ ጥያቄዎች

- ሰዎች ስለ እኔ አመራር ምን ይሉ ይሆን?
- ባለቤቴና ልጆቼ መላው ቤተሰቤ ስለ እኔ ምን ይላሉ?
- እግዚአብሔርስ ስለ እኔ ምን ይል ይሆን?
- እኔስ ስለ ራሴ ምን እላለሁ? ሁሉም አለኝ አንዳች አያስፈልገኝም ባይ ነኝ ወይ?
- ለአሁኗ ቤተ ክርስቲያን የውስጥ ችግር ምን መደረግ አለበት ይላሉ?
- መሪዎች በጋራና በተናጠል ሲመሩ ልዩነቱን፥ ጥቅምና ጉዳቱንም ይዘርዝሩ?

የግርጌ ማጣቀሻ (Notes)

1. *Henery Clarence Thiessen, "Systematic Theology", (Grand Rapids, Michigan,1993), P.418.*
2. *Ibid, P. 419.*
3. *Neil Braun, "Laity Mobilization", (William E.Pub. USA, 1971), P.127.*
4. *Ibid, P. 132.*
5. *Ibid, P. 113*